# ጋብቻና የትዳር ሚስጢር

በመጋቢ እንድርያስ ሐዋዝ

770 7th St. East

St. Paul, MN 55106

Phone 651-772-0216

ጋብቻና የትዳር ምስጢር
© ሐምሌ 2001 በእንድርያስ ሐዋዝ
የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው
ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ

Wedding and the Secret of Marriage
© 2009 By Endiryas Hawaz
All Rights Reserved
United States of America

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከታች ከተመለከቱት የአማርኛና የእንግሊዘኛ ትርጉሞች ነው።**

All Scripture Quotations are from the Bible
In Amharic © **United Bible Society 1962**
**AND**

**NIV** New international version

**KJV** King James version

**NKJV** New King James version

# ማውጫ

| ምዕራፍ | ገጽ |
|---|---|
| ፩. የጋብቻ አይነቶች | 1 |
| ፪. የትዳር ውድቀት ጅማሬ | 21 |
| ፫. ጋብቻና አላማው | 39 |
| ፬. ትዳር ያለ ፍቺ | 59 |
| ፭. በትዳር ውስጥ ያለ ግጭትና መፍትሄው | 75 |
| ፮. ትዳርና የቤተሰብ አመራር | 99 |
| ፯. የትዳር ማጣፈጫ ቅመሞች | 113 |

# መግቢያ

ይህች መጽሐፍ የጋብቻን ሥርና መሰረት ተንትኖ ለማስ ተማር የተጻፈች ሳትሆን ባለፉት ጥቂት አመታት በቤተ ክርስትያናችን ውስጥ ለጋብቻ የሚዘጋጁትን ተጋቢዎች ሳስተምር ይህ ትምህርት በመጽሃፍ መልክ ቢዘጋጅ ለሁልጊዜ የሚጠቅም መሳሪያ ይሆናል የሚል የተደጋገመ አስተያየቶች ስለተሰጡኝ ከአንድ አጥቢያ ቤተክርስትያን አለፍ ባለ መልኩ ሌሎችንም እንደሚረዳ በማመን የተጻፈች ናት።

የዚህች መጽሐፍ ዋና አላማ በትዳር ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔር ሚስጢር በመግለጽ ፣ በእግዚአብሔር ሃሳብ ላይ የተመሰረተ ጋብቻ ምን እንደሚመስል ለማሳየትና የተጋቡ ሰዎች በቂ ትምህርት ከማጣት የተነሳ ሲቸገሩ ስለማይ አስፈ ላጊውን እውቀት ለመስጠት ነው።

እኔና ባለቤቴ ማርታ ታደስም በትዳር ውስጥ ለአስራ ዘጠኝ አመት ያህል ስንቆይ በከፍታና በዝቅታ በደስታና ሀዘን ውስጥ ታላቁ እረኛ ረድቶን አራት ልጆች ለማድረስ ያበቃንን እግዚአብሔር አምላካችንን እያመሰገንኩ በህይወት ገጠመኝ ውስጥ ያሉትን እውነታዎች ካሳለፍነው ልምድ በጥቂቱ አካ ፍላለሁ።

በመልእክቴ ውስጥ ሦስት መሰረታዊ ነገሮችን እን ስቻለሁ። አንደኛ ባልና ሚስት የጌታን አላማ በዚህ ምድር ላይ በህይ ወታቸው ፈጽመው ለማለፍ በጌታ ክሁርና ቅዱስ አላማ በትዳር ውስጥ ገብተዋል። ይህ የጌታ አላማ የሚፈጸመው ባልና ሚስት በውህደት መኖር አስከ ቻሉ ድረስ ብቻ ነው። በዚህ ምክንያት ለምን አንድ እንደሆኑ ፣ እንዴት አንድ እን ደሆኑና አንድ የመሆን ሂደት ምን እንደሆነ በሚገባ ማወቅና

መረዳት ይገ ባቸዋል። የኔም የመጀመሪያ መልእክቴ በእነዚሀ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ይሆናል።

ሁለተኛ ምንም እንኳን ባለትዳሮች ለአንድነት በውህደት መሞር ዋና አላማቸው ቢሆንም በመካከላቸው ልዩነት እንዳላቸው መዘንጋት አይገባቸውም። እነዚሀ ልዩነቶች በጾታቸው በአፈጣጠራቸውና ሊለውጡ በማይችሉአቸው ማንነታቸው ላይ ያተኮረ ስለሆነ በትዳረቸው ውስኖ የተለያዩ አለመግባባቶችና ግጭቶች መኖራቸው ግልጽ ነው። ታድያ ይሀንን ልዩነት ምን እንደሆነ ያለማወቅ ችግርና ችግሩንም እንዴት መፍታት እንዳለባቸው ባለማወቅ ምክንያት ቀላልና በጊዜው ቢፈቱ ለትዳሩ የሚጠቅሙ አለመግባባቶች ሁሉ ወደ ሌላ አቅጣጫ በመሄዳቸው ትዳሩን ለችግር ያጋልጡታል። በዚሀ ጉዳይ ላይ ሰፋ ያለ ማብራሪያ በመስጠት አለመግባባቶች ምን እንደሆኑና ግጭቶች በሚነሱበት ጊዜ እንዴት በቀላሉ መፍታት እንደሚቻል ለማሳየት ሞክሬአለሁ።

በሦስተኛ ደረጃ ልዩነቶች እንደተጠበቁ ሆነው በአንድነት ለመኖር የቤት አስተዳደር ምን እንደሆነ ማወቅ አስፈላጊ ነው። የአንድ ቤተሰብ አስተዳደር ምን እንደሚመስልና መጽሐፍ ቅዱሳዊ የቤተሰብ አስተዳደር ባለበት ቦታ ላይ ሁሉ ትዳር ጤነኛና በየጊዜው ወደ እድገት ማምራት የሚችለው እንዴት እንደሆነ በማውሳት የባልንና የሚስትን ድርሻ ምን እንደ ሆነ በማሳየት ጠቃሚ ምክር ለግሻለሁ።

በዚሀ ጽሑፍ እንደምትባረኩ በማመን ጽሑፌን በጌታ ላይ በመታመን በመንፈስ ቅዱስ የተቀባና የብዙዎች ባለትዳሮችን ሀይወትና ኑሮ የሚለውጥ ይሆን ዘንድ በታላቅ ጸሎትና እክብሮት ለአንባቢዎች አቀርባለሁ።

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ ይህችን መጽሃፍ ለመጻፍ ምክንያት የሆኑኝን ባለፉት ሰባት አመታት ውስጥ የጋብቻ ትምህርት ያስተማርኳቸውን የቤተክርስትያናችንን የጋብቻ ተማሪዎቼን በሙሉ ለመስግን እወዳለሁ። ከትምህርቱ በኋላ ይህ ትምህርት በመጽሐፍ መልክ ብታቀርበው ብዙዎች ሊጠቀሙ ይችላሉ በማለት በየጊዜው ያበረታቱኝን ሁሉ ጌታ ይባርካቸው ለማለት እወዳለሁ።

ይህንችን መጽሃፍ ከጻፍኩ በኋላ የጽሁፉን የታይፕ ስህተቶችንና የቃላት ግድፈቶች አርማት የሰጠችኝን ለውድ ባለቤቴ ማርታ ታደሰ ከሁሉ አስቀድሜ ከልብ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ከእኔ ጋር በሙሉ ጊዜ አገልግሎት የተጠመዱትን ወንድሜ ወንጌላዊ የሃንስ በለጠንና መጋቢ አስጢፋኖስ አለሙን ከልብ አመስግናለሁ። በቤተክርስትያናችን በድቁና አገልግሎት ውስጥ አብረውኝ የሚያገለግሉትን እህት ጽጌረዳ ደምቤን ፣ እህት አንቀጽና ወንድም ታምሩ ይገዙን ከልብ አመስግናለሁ። እንዲሁም በቤተክርስትያናችን አገልጋይ የሆኑትን ወንድም ያሬድ ካሳን እህት አደይ አበበን ፣ ወንድም ሙሉጌታ አርአያን ወንድም ብርሃነመስቀልና ባለቤቱ ሃና አሰፋንና ወንድም አሸናፊን ከልብ አመስግናለሁ። በመጨረሻም የመጽሀፉን ሽፋን ባማረ ዲዛይን ጊዜውን ሰጥቶ በመስራት የረዳኝን ፓስተር መስፍን ማሞን ከልብ አመስግናለሁ።

ከሁሉም በላይ አስጀምሮ ያስጨረሰኝን ታላቁን አዳኝ ጌታ ኢየሱስን በምስጋና ላይ ምስጋና በክብር ላይ ክብር ለእርሱ ይሁን እላለሁ።

፩

# የጋብቻ አይነቶች

በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተጻፉ ሦስት የጋብቻ አይነቶች አሉ። አንደኛውና የመጀመሪያው ፍጹም የነበረና ከፍጹምና የወደቀ የምንለው የጋብቻ አይነት ነው። ይህ አዳምና ሄዋን በኤደን ገነት ከሃጢአት ውድቀት በፊት የነበራቸው የጋብቻ አይነት ነው። ሰው ንጹህ እንጂ ፍጹም ሆኖ አልተፈጠረም። ምክንያቱም ፍጹም ከነበረ ሊሳሳት አይችልም ነበርና ነው።

ከዚህ በታች ያለውን መልእክት ለመረዳት እንድንችል ግን ከንጹህ ይልቅ ፍጹም የሚለው ቃል ለብዙ ሰው ስለሚገባ ጋብቻዎቹ ምን እንደነበሩ ለማየትና ሃሳቡን በትክክል ለመረዳት እንድንችል ብቻ ንጹህ ከሚለው ቃል ይልቅ ፍጹም የሚለውን በመጠቀም እናየዋለን።

ሁለተኛው የጋብቻ አይነት ከፍጹምነት የወደቀና ወደ ፍጹምነት የሚያድገው አይነት ነው። ይህም ሰው በሃጢአት ከወደቀ በኋላ የመጣና ከአዳም ውድቀት እስከ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ሁሉ ያለውን ጋብቻ ያካልላል።

ሦስተኛው የጋብቻ አይነት ፍጹም የሆነና ለዘላለም ፍጹም የሚሆን ጋብቻ ነው። ይህም በክርስቶስ እየሱስና በቤተ

ክርስትያን መካከል የሚደረግ የጋብቻ አይነት ነው። የበጉ ሰርግ እስኪሆን መንፈስ ቅዱስ ቤተክርስትያንን ለሰርግ ቀን እን ድትዘጋጅ ከአብ ዘንድ ስጦታን ይዞ መጥቶአል። ይህች ሙሽራ በሰርጉ ቀን ፍጹምና ቅድስት ንጽህት ሆና ያለ ነቀፋ እስክትሆን ድረስ መንፈስ ቅዱስ ለሙሽራው ለኢየሱስ ያዘጋጃታል።

የመጀመሪያው ጋብቻ በኤደን ገነት በራሱ በእግዚአብሔር አጋቢነት በመጀመሪያዎቹ የሰው ዘር ፍጥረታት በአዳምና ሄዋን መካከል የተደረገ ነው። ይህ ጋብቻ በአይነቱ የመጀመሪያና አስደናቂ የሆነ የጋብቻ አይነት ነው። ልዩ የሚያደርጉት ብዙ ነገሮች ቢኖሩም ከጥቂቶቹ መካከል ለማየት አጋቢው ራሱ ፈጣሪው መሆኑና ጋብቻው የተፈጸመው በኤደን ገነት ውስጥ ምስክር እግዚአብሔር ብቻ ሆኖ ገና ሰው በሃጢአት ሳይወድቅ የተደረገ መሆኑ ነው።

እነዚህ ነገሮች ሁሉ ይህንን የመጀመሪያ ጋብቻ ከሌሎቹ ሁለት የጋብቻ አይነቶች ለየት ያደርጉት እንጂ ጋብቻው እሁ ንም በአንድ ወንድና በአንድ ሴት መካከል ብቻ የተደረገ ነበር። አዳምና ሄዋን ገና ሃጢአት ወደ አለም ሳይገባ የተጋቡ ስለነበር ጋብቻቸው ያለ ሃጢአት ነበረ። በዚህ ምክንያት ተጋቢዎቹ በፍጹም ንጽህና ያለ አንዳንች ችግር በደስታ ይኖሩ ነበር።

ከዚህም በላይ ይህ ጋብቻ እግዚአብሔር ትክክለኛ ጋብቻ ምን እንደሚመስል ያሳየበት ለጋብቻዎች ሁሉ አርአያ የሆነ የጋብቻ አይነት ነው። ይህም ምሳሌነቱ እግዚአብሔር አባት ሆኖ ሄዋንን ከሰራት በኋላ ለአዳም እንደ አባት አምጥቶ ማስረከቡና ሄዋንንም ሰርቶ ለአዳም የምትመቸው ረዳት አድርጎ ማምጣቱ ነው።





ባሬም ለጋብቻ የእግዚአብሔር ሃሳብ ይህ ነው። ልጆች በቤተሰብ ተኮትኩተው ለትዳር ፣ ለአገርና ለወገን የሚመቹና የሚጠቅሙ ሆነው በባህሪይና በእውቀት መዘጋጀት አለባቸው። ትልቁ ሥራ የሰውን ህይወት ወይንም ባህሪይ መስራት ነው። ባህሪው የተሰራን ሰው ለምንም ነገር ማብቃት ይቻላልና።

እግዚአብሔር ከአዳም ውስጥ አጥንትን አውጥቶ ስለነበር አዳም ባያት ጊዜ የራሱ አድርጎ ሊቀበላት አልተቸገረም። እን ደውም ይህች አጥንት ከአጥንቴ ስጋም ከስጋዬ ናት እርስዋ ከወንድ (ከእኔ) ተገኝታለችና ሴት ትባል አለ። በእብራይስጡ ሴት የሚለው ቃል አይሻ (Isha) ማለት ሲሆን አይሻ ማለት በጾታ ብቻ ከእኔ የምትለይ ሰው ማለቱ ነበር።

እዚህ ላይ እግዚአብሔር ለሙተው የፈለገው መልእክት አለ። እሱ ሄዋንን ለአዳም ሰርቶ እንዳመጣለት ትክክለኛ ትዳር ጅማሬው በጋብቻ ውስጥ ሳይሆን በጓንዋንና በጓኑን በሚያሳድጉ ወላጆች ላይ መሆኑ ነው። ይህም ከፍተኛው የወላጅ ሃላፊነት ነው።

በመዝሙር 127፥3-5፦ *«ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው። ... በሃያል እጅ እንዳሉ ፍላጾች የጎልማሰነት ልጆች እንዲሁ ናቸው። ከአነርሱ ዘንድ ምኞቱን የሚፈጽም ብጹእ ሰው ነው»* ይላል። ብዙ ሰው ልጆቹ የእግዚአብሔር ስጦታ እን ደሆኑ በማመን በስጦታው ደስ ይሰኛል። ይሁን እንጂ ስጦታው የት መድረስ እንዳለበት ምን ግብ መምታት እንዳለበት ጦሩ ያለው በወላጅ እጅ መሆኑን አያስተውልም። ዛሬ ብዙ ልጆች የተጣመሙ ቀስቶች ሆነው ያደጉት በወላጆቻቸው እጅ ነው። ጠማማ ቀስት ቢወረውሩት ግቡን እንደማይመታ ተጣሞ ያደገ ንም ልጅ ወደተፈለገው አይነት ትዳር ፣ መንፈሳዊ አገልግሎትና በህብረተሰብ ውስጥ ወዳለ የአመራር ሃላፊነት ማብቃት ያስቸግራል። በዚህ ጥቅስ ላይ የሚያስገርም ቃል ተጠቅሶአል።

ይህም በቁጥር አምስት ላይ ያለው ነው። እንዲህ ይላል *«ከአነርሱ ዘንድ ምኞቱን የሚፈጽም ብጹእ ነው»።*

እግዚአብሔር ልጆችን ለወላጆች ስጦታ አድርጎ ሲሰጥ ይህንን የተበላሸ አለም እንደ ውጊያ ቦታ ወላጆችን እንደ ጦረኛ ፣ ልጆችን ደግሞ እንደ ፍሮር አድርጎ ነው። ትውልድ የሚዋጀው በልጆች ላይ በሚነጣጠር አላማ ነው። ልጆቻችንን ለምን አላማ ለምን ቁም ነገር እያስተማርናቸው እንዳለን የት ወርውረናቸው ምን እንደሚመቱልን ማወት ያለብን እኛ የእግዚ አብሔር ህዝቦች የሆንን ወላጆች ነን።

በምእራቡ አለም በጋብቻቸው ቀን ሙሽራውና ሙሽራይቱ የሚተያዩት በቤተክርስትያን ውስጥ ነው። በቤተክርስትያን ውስ ጥም የሙሽራይቱ አባት ልጁን ይዞ ከመጣ በኋላ ያሳደጋትን የደከመባትን ልጁን ለሙሽራው በህዝብ ፊት ያስረክባል። ይህ ባህል መልካም ምሳሌነት አለው። አባት ለቁም ነገር እስከትበቃ ድረስ ልጁን መክሮ አስተምሮ ካሰደገ በኋላ በትዳርዋ ውስጥ ጥሩ ሚስትና ፍሬያማ ለመሆን በቅታለች ሲል ለአዲሱ የትዳር ጓደኛዋ ያስረክባል።

ልክ እንደዚህ አይሁን እንጂ በአገራችንም ቢሆን ልጅህን ለልጁ ተብሎ ተጋቢዮቹን የሚያገናኙ ወላጆች ነበሩ። ወላጅ የደከመባትን ልጁን ለማን እንደሚሰጥ አይቶ አጣርቶ ይሰጥ ነበር። ይህም ወላጅ የማሳደግ ብቻ ሳይሆን የማስረከብም ሃላ ፊነት እንደነበረው ያሳያል።

ታድያ ይህን ስል ባሬም ልክ እንደባው ወላጆች ያለ ልጆች ፈቃድና ምርጫ ልጆቻቸውን በማገናኘት ትዳር ይመሰረት ማለቴ አይደለም። ነገር ግን ያም የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ እን ዳለው ለማሳየት ነው እንጂ።





በዚህ ዘመን የሚጋቡ ወጣቶች ምንም የወላጅ ምክር አስተያየትና ውሳኔ ሳይጠይቁ በትዳር ውስጥ መግባታቸው ሊታ ሰብበት የሚገባ አሳሳቢ ጉዳይ ነው። እዚህ ላይ ሚዛን መጠ በቅ ያለብን ይመስለኛል።

ይህም የወላጆች ድርሻ ምን ድረስ እንደሆን ፣ የልጆችም ድርሻ ምን ድረስ እንደሆን ታውቶ ወላጅም እኔ ያልኩህን ካላ ገባህ ሞቼ እገኛለሁ እንዳይል ልጅም እኔ ያመጣኋትን ምንም ትሁን ተቀበል እንዳይል መካከል መንገድ ላይ መጥተው ወላጅ ለልጁ የሚጠቅመውን ምክር ማስጠንቀቂያና መምሪያ የመስጠት ሙብቱ ሳይገፈፍ ፣ ልጅም ወላጅ የሰጠውን ይሁን እስ ያመጣትን ለማግባት የወደዳትን ወይንም የወደደችውን የማግ ባት መብታቸው ሳይገፈፍ እንደ እግዚአብሔር ህዝብ በመመ ካከር የጌታን ፈቃድ ለማወቅ መሞከሩ ከብዙ ጥፋት ያድናል። ብዙ ምክር ባለበት በዚያ ድል አለና።

የመጀመሪያው የአዳምና ሄዋን ጋብቻ ላይ እግዚአብሔር ሄዋንን ሰርቶ ለአዳም ሲያስረክብ አዳም ደግሞ እግዚአብሔር የሰጠውን ልክ ነው በማለት አጥንቷ አጥንቱን መሳይ መሆኑን አረጋግጦ እንደወሰደ ወላጅ የደከመበትን ልጅ ለማን እንደ ሚሰጥ መጠየቁ ተገቢ ሆኖ ሳለ ልጅም የመጣለት አጥንት ከአጥንቱ መሳይ መሆንዋን ፈትሾ መውሰዱ ትልቅ ማስተዋል ነው።

የባሬው ጋብቻ መሰረቱና አዝማሚያው የማያምር መሆኑን በማየት ወጣቶቻችን በገዛ ምኞታቸውና ባልበሰለ አእምሮአቸው ወደዚህ ትልቅ የጋብቻ ሃላፊነት ሲገቡ ስልጣኔ መስሎን ወላጆች ዝም ብለን እንዳናይ ፣ የወላጅ አስተዋጽኦ በትዳር ላይ እጅግ ከፍተኛ መሆኑን ለማሳሰብና ወጣቶችም ያለፈቃዳቸው በወላጅ ፍላጎት በበር በዝና ወይም በስም ላይ የተመሰረተ ጋብቻ ውስጥ ከማይወዱት ሰው ጋር ለመኖር እንዳይገደዱ ሚዛኑን

በጠበቀ መልኩ ልክ እንደ እግዚአብሔር ቃል ቤተሰብን እን መሰርት ነው።

መጽሃፈ ምሳሌ በመጨረሻው ምእራፍ ላይ የጥበብ ትምህርትን የዘጋው በጥበበኛና በታታሪዋ እግዚአብሔርንም በምትፈራው ሴት ነው። ለምን ይሆን እግዚአብሔርን በምትፈራው ሴት መሰሎ የዘጋው? አንደኛ ጥበብ የተሞላ መልካም ሁብረተሰብ ምንጩ ጤነኛ ቤተሰብ ስለሆነና ሁለተኛም በቤተሰብ ውስጥ በልጆች ላይ ተጽእኖ የማምጣትም ሆነ መልካም ምሳሌ የመሆን ትልቅ ድርሻ ያላት ሴት በመሆንዋ ነው።

እዚህ ላይ የቤተሰብ ሃላፊነት የተጣለው ሴት ላይ ብቻ ነው ለማለት ሳይሆን ሴቶች በአብዛኛው ልጆችን ገና በህጻንነታቸው የህይወት ትምህርት የሚማሩበት እድሜአቸው ላይ ሳሉ ብዙውን ጊዜያቸውን የሚያጠፉት ከእናታቸው ጋር በመሆኑ የእናቶች ሃላፊነት ከፍተኛ መሆኑን ለማሳየት እንጂ ልጅን ማሳደግ የወንዶች ሃላፊነት አይደለም ለማለት አይደለም።

በምሳሌ 31፥10 *«ልባምን ሴት ማን ሊያገኛት ይችላል»* ይላል። ይህ ልባም የሚለውን ቃል ሌሎች ትርጉሞች ምግባረ መልካም የሆነችውን ሴት ማን ሊያገኛት ይችላል ብለውታል። ታዲያ መልካም ምግባር ከየት ይወረሳል? መልሱ በአብዛኛው ከቤተሰብ ለመሆኑ አጠያያቂ አይመስለኝም። ልጁንም ልጅትዋንም አይቶ ቤተሰብ እንዴት እንዳሳደጋቸው መገመት አያዳግትም። ዞሮ ዞሮ ትልቁ ሃላፊነት በአሳዳጊ ቤተሰብ ላይ የተጣለ መሆኑ ግልጽ ነው።

የዛሬው ቤተሰብ ልጁን ምን እንሚያበላ ምን እንደሚያለብሰና የትኛው ትምህርት ቤት እንደሚያስተምር እንጂ የልጁ ባህሪይ ምን እንደሚመስል በቅርብ የሚከታተል ወይንም የሚገደው ያለ አይመስልም። በእኔ ግምት ለትምህርት ቤትና ለኑሮ የሚታሰበውን ያህል ለልጆቻችን ባህሪይ መቅረጽ እግዚ





አብሔርንም መፍራት እንዲማሩ አስፈላጊውን ትምህርትና የቤተሰብ ምሳሌነት ማሳየት ቤትንም ሁብረተሰብንም ቤተክርስትያንንም ከብዙ ጉዳት ያድናል ብዬ አምናለሁ።

ወደ ትዳር አለም ለሚገቡ ወጣቶች ምክር አለኝ። ወጣቶች ወደ ትዳር አለም ውስጥ ከመግባታቸው በፊት የሚያገቡትን ሰው መንፈሳዊ ህይወት ብቻ ማየት ሳይሆን ባህሪው ምን እንደሚመስል ማወቅ ፤ ማጥናትና ከዚህም በላይ በሚገባ መፈተን እጅግ አስፈላጊ ነው። እመልና ጅራት ወደ ኋላ ነው እንዲሉ የሰውን ባህሪይ በቀላሉ ማወቅ ስለማይቻል ወደ ትዳር ከመግባታቸው በፊት ሰፋ ያለ ጊዜ ሰጥቶ መጠናናቱ ይጠቅም ይሆናል እንጂ አይጎዳም።

ይህን ስል የእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነውን ትዳር ካየነው ባህሪይ የተነሳ አንተው ማለቴ ሳይሆን ወደ ትዳር ውስጥ ያለምንም ዝግጅት ዘው ብሎ ከመግባትና ከመደናገጥ አስቀድሞ አውቆ ቢቻል ከትዳሩ በፊት ባህሪው የሚለወጥበትን መንገድ መሞከር ካልተቻለም ያንን ባህሪይ የሚሸከም ትከሻ አዘጋጅቶ መግባቱ ከጊዜ በኋላ ከሚነሳ ጸጸትና ምሬት ያድናል።

## ትዳርና የኤደን ገነት

የኤደን ገነትን ፍጹም ጋብቻ የተለየና ፍጹም የሚያደርጉት ሦስት መሰረታዊ ነገሮች አሉ። እነዚህም ነጥቦች በትዳር ውስጥ ላሉ ሁሉ ትምህርት የሚሰጡ ናቸው። አንደኛው የኤደን ገነት ዛፍ ሁለተኛው የእግዚአብሔር መገኘትና ሦስተኛ አዳምና ሄዋን ተላብሰውት የነበረው ጸጋ ናቸው።

1. የኤደን ገነት ዛፍ (እንደ እግዚአብሔር ቃል ምሳሌ)

የኤደን ገነት ዛፍ በአዳምና ሄዋን ጋብቻ ውስጥ አይነተኛ ሚና የተጫወተችና በህይወት ለመቆየታቸውም ለመውደቃቸውም ምክንያት የነበረች ዛፍ ናት። እግዚአብሔር አምላክ ይህችን ዛፍ በኤደን ገነት መካከል ሲያስቀምጣት በአላማና በምክንያት ነበር። ስለ ዛፊትዋ ከማየታችን በፊት ዛፊትዋ ስለተተከለችበት የኤደን ገነት ስለተባለው ቦታ ጥቂት ነገር እን ይ።

በዘፍጥረት 2፥8 ላይ *«እግዚአብሔር አምላክም በምስራቅ <u>በኤደን ገነትን ተከለ</u> የፈጠረውንም ሰው ከዚያው አኖረው»* ይላል። ከዚህ ክፍል እንደምንረዳው እግዚአብሔር ዛፊቱን ከመትከሉም በፊት የሰራው የኤደን ገነትን ነበር። ኤደን ምንድን ነው? እግዚአብሐር ለምን የኤደንን ገነት በቅድሚያ ተከለ? ሰውንስ ለምን በኤደን እንዲኖር አደረገው? እነዚህ ጥያቄዎች ሁሉ አስፈላጊና መመለስ የሚገባቸው ናቸው ፤ ይሁን እንጂ አላማዬን የሚደግፉትን ጥቂቶቹን ብቻ ላንሳ።

ኤደን ማለት ደስታ ማለት ሲሆን የኤደን ገነት ማለት ደስታ ያለበት የመናፈሻ ቦታ ማለት ነው። እግዚአብሔር አዳምና ሄዋንን ከመፍጠሩ በፊት በደስታ የሚኖሩበትን ገነት ነበር ያዘጋጀላቸው። ልክ እንድ ህጻን ሳይወለድ ወላጆቹ የልጁን አልጋ ፣ ልብስና የተለያዩ ነገሮች እንደሚያዘጋጁ እግዚአብሐርም ለልጆቹ አንድም ነገር ሳይጎላቸው በደስታ የሚኖሩበትን ቦታ አዘጋጅቶላቸው ነበር።

እግዚአብሐር አምላክ ሰውን በኤደን ገነት ሲያስቀምጠው ሁለት ሥራ ሰጥቶት ነበር። አንደኛው እንዲያበጃት ሲሆን ሁለተኛው እንዲጠብቃት ነው። ይህ እንዲያበጃት የሚለው ቃል ማበጀት ወይንም መስራት ማለት ሲሆን ሁለተኛው የኤደን ገነት ትእዛዝ እንዲጠብቃት ነበር። መጠበቅ የሚለው ቃል መጋረድና መቆየት የሚል ትርጉም አለው።





ምንም እንኳን የኤደን ገነት ምንም የሚጎላት ባትመስልም እግዚአብሐር ግን ሰውን ያለምንም ሥራ አልተወውም። ይህ ሥራ ምን እንደሆነ ለመገመት ቢያዳግትም ሰው እግዚ አብሐር የሰጠውን የደስታ ስፍራ የሚጠብቀው በሥራ እንደሆነ ማየት ግን አያስቸግርም።

እንደ እውነቱ ከሆነ ትዳር የደስታ የበረከትና የፌውስ ቦታ ነው። ነገር ግን አንድ ልብስ ሰፊ ልብሱን የሚሰፋው እንደሚለብሰው ሰው ርዝመትና ስፋት የሚፈልገውን አይነት ዲዛይን መርጦ እና ለክቶ እንደሆነ ሁሉ እግዚአብሔር ለባለትዳሮች ተሰፍቶ ያለቀን ልብስ ሳይሆን የሚሰፋውን ልብስ ጣቃ ወይንም ብትን ጨርቅ ነው የሚሰጠው። በምን አይነት ልክና መልክ ወይንም ዲዛይን መሰራት እንዳለበት የሚወሰኑት ግን ተጋቢዎቹ ናቸው።

ለምሳሌ በጌታ ኢየሱስ ያገኘነው ደህንነት በነጻ የተገኘ ሙሉ የደስታ ህይወት ቢሆንም ይህንን ህይወት ግን በሙላት ለመኖር ወይንም ላለመኖር ምርጫው የአማኞቹ ነው። ይህንንም ህይወት በጸሎት በቃሉና በቅዱሳን ህብረት የመጠበቅ ግዴታ ያለባቸው አማኞቹ ናቸው።

ልክ እንደዚሁ ተጋቢዎች ሁሉ ወደ ትዳር አለም ሲገቡ ወደ ኤደን ገነት ወደ ታላቅ የደስታ ህይወት ይገባሉ። ይሁን እንጂ ብዙ ሰው የተሰጠውን ደስታና በረከት እንጂ ግዴታውን ወይንም ትዳር ልንጠብቀው ልንንከባከበው የተሰጠን ሥራ መሆኑን ይዘነጋል። በዚህ ምክንያት ያ ያማረ የኤደን ገነት የሚመስለው ትዳር በጥቂት ጊዜ ውስጥ ተበላሽቶ የሃዘንና የትካዜ የብስጭትና የመለያየት ቦታ ይሆናል።

በሉቃስ 15 ላይ የጠፋው ልጅ ከአባቱ የተቀበለው ያልለፋበት ያልደከመበት ታላቅ በረከት ነበር ። ይሁን እንጂ ይህ ወጣት ያልተረዳው የተሰጠው ነገር በረከት ብቻ ሳይሆን ሃላፊነት መሆኑን ነበር። ይህ ወጣት በነጻ ያገኘውን በረከት ሊነግድበት ሊያተርፍበት ሲገባ እሱ ግን በተነው። የሚያልቅ አልመሰለውም። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ያለውን በትኖ ሲጨርስ ከአርያ እሰር ሊበላ ይመኝ ነበር። የሚሰጠው ግን አልነበረም።

በትዳርም ውስጥ ያለን ፍቅር ከጌታ ዘንድ የተሰጠን ትልቅ ሃብት ነው። ይህንን ትልቅ ሃብት ግን ዛሬ ብዙ ተጋቢዎች ከእግዚአብሔር የሰጣቸው ሃብት መሆኑን በመዘንጋት በትዳር ውስጥ ያለውን የአፍላ ፍቅር ደስታና በረከት ሊጠብቁትና ሊንከባከቡት ሲገባ ይበትኑታል። ከትዳር ጓደኛቸው የሚያገኙትን ፍቅር ፣ ትእግስት ፣ ሥራና እንክብካቤ ሁሉ ያለ አግባብ ይበትኑታል። ባለቀ ጊዜ ግን ይመኛሉ የሚሰጣቸውም የለም። ትዳራችን ከጌታ የተሰጠን አስደናቂ በረከት ነው። ይሁን እንጂ የተሰጠንን በረከት የመጠበቅ የመንከባከብ ሃላፊነት የእኛ የተጋቢዎች ነው።

ታድያ ይህንን የትዳር ደስታና በረከት የምንጠብቀው እን ዴት ነው? የሚል ጥያቄ በአንባቢዎች በንድ መነሳቱ ስለማይቀር ለጊዜው አንዱን ብቻ ለንሳ። መጀመሪያ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ከሰጠው ትልቅ ሃብትና በረከት መካከል አንዱ የሆነው የሰው ፈቃድ ነው። የሰው ፈቃድ የከበረና ልንጠነቀቅለት የተገባ ትልቅ ሃብት ነው።

እግዚአብሔር አምላክ ከሰው ጋር ባለው ህብረትና አን ድነት ውስጥ ሁሉ የቱንም ያህል ሰውን የማዳንና የመርዳት ሃሳብ ቢኖረውም ባደረገው ነገር ውስጥ ሁሉ ግን ያልጣሰው ነገር ቢኖር የሰውን ፈቃድ ነው።





ከሰማይ ወርዶ ከድንግል ማርያም እንደ ሰው ሊወለድ በማይገባው ቦታ ተወልዶ ፣ የሰዎችን ሃጢአት ሁሉ በመስቀል ላይ ተሸክሞ ዋጋውን ሁሉ ከከፈለ በኋላ ለሰው ልጆች የሰጠው ጥሪ ማንም ሊከተለኝ ቢወድ ወደ እኔ ይምጣ ነው እንጂ ይህ ንን ያህል ዋጋ ከፍያለሁና በግድ እንድታምኑኝ አላለም። ነገር ግን የዋህና ትሁት ሆኖ በሰው የልብ ደጅ ላይ ቆሞ አንኳኳ እንጂ የማንንም ደጅ ሰብሮ አልገባም።

እኛው ታመን ለመፈወስ ፈዋሽ አምላካችሁ እኔ ነኝ እያለ ይለምናል እንጂ ማንንም አስገድዶ አይፈውስም። እግዚአብሔር አምላክ ጌታና ትልቅ ሆኖ እያለ ማንንም ግን አይንቅም። ጥፋትን ሲያይ እንኳን በረከትና መርገም ሞትና ህይወት በፊትህ ነው በረከትንና ህይወትን ምረጥ እያለ ይለምናል እንጂ ማንንም አስገድዶ አያድንም።

አንዱ በቤተሰብ ላይ የሚታየው ትልቅ ችግር ቢኖር ይህ ይመስለኛል። አንድ ባል ሚስቱን ካገባት በኋላ ሊጠብቅላት የሚገባው ነገር ቢኖር ፈቃድዋን ሆኖ ሳለ ወይም አንድ ሚስት ባልዋን ካገባችው በኋላ ልትጠብቅለት የሚገባው ነገር ቢኖር ፈቃዱን ሆኖ ሳለ ይህንን ባለማድረግ የትዳር ጓደኛቸውን ፈቃድ በመጣስ ባልና ሚስት ሆድና ጀርባ መሆን ይጀምራሉ።

ይህንንም የሚጀምሩት አንደኛው ክፍል የሌላውን ፈቃድ እየጣሰ ለቤተሰቡ የሚጠቅም ነው ፣ ወደፊት ይገባሃል ፣ ይገባሻል በማለት ማንኛውንም ውሳኔ ትክክል ነኝ በማለት ያለ ትዳር ጓደኛው ፈቃድ ወይንም በማስገደድ በሚያደርግበት ጊዜ ነው። ይህንን የሚያደርገው ሰው ለጊዜው ያሰበውን ነገር ማድረግ ይችል ይሆናል ፤ የትዳር ባልንጀራውን እምነትና ፍቅር ግን ሳያውቅ እየጣ ይሄዳል። በትዳር ውስጥ የሚወሰነው ማን ኛውም ውሳኔ የሁለቱንም ፈቃድ ያካተተና ሁለቱም ተስማምተው እስካደረጉት ድረስ ብቻ ነው ትዳሩ ጤነኛ

የሚሆነው። በአንዱ ፈቃድ ላይ ብቻ የተወሰነ ህይወት መኖር ከጀመሩ ትዳሩ ቀን ቆጥሮ መውደቁ የማይቀር ነው።

## 2. የእግዚአብሔር መገኘት

የኤደንን ገነት የደስታ ስፍራ ያደረገው የዛፉና የሚበላው ፍሬ ወይንም የተለያዩ ወንዞች መኖራቸው ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር መገኘት ነበር። ይህ ስፍራ እግዚአብሔር በተለየ መልኩ መገኘቱን ያስቀመጠበትና አዳምና ሄዋንም የሚያውቁት ነበር። እግዚአብሔር አምላክም መገኘቱን በሁለት መንገድ ለአዳምና ሄዋን ይገልጥላቸው ነበር።

አንደኛ በድምጹ ሲሆን ሁለተኛም በቃሉ ነበር። በዘፍጥረት 3፥8 ላይ *«ቀኑ በመሸ ጊዜ የእግዚአብሔር የአምላክን ድምጽ ከገነት ውስጥ ሲመላለስ ሰሙ።»* አዳምና ሄዋን የእግዚብሔር የአምላካቸውን መገኘት ወደ አመሻሽ ላይ ለየት ባለ መልኩ ይለማመዱ የነበረው ድምጹን በመስማት ነበር።

እግዚአብሔር ራሱን የሚገልጽበት መንገድ አንዱ መናገሩ ወይም ድምጹን ማሰማቱ ነው። ለዚህ ነው የእብራውያን ጸሃፊ በእብራውያን 1፥1-3 ባለው ክፍል ላይ እግዚአብሔር በብዙ አይነት መንገድና ብዙ ጊዜ በነቢያቱ ሲናገር እንደነበረና በኋላ ግን የክብሩ ነጸብራቅና የባህሪዩ ምሳሌ በሆነው ሁሉን በስልጣኑ ቃል ደግፎ በያዘው በእየሱስ በመጨረሻ ተናገረን የሚለው።

በሀጸአት 24 ላይ ከግብጽ ምድር ድንቅና ተአምር ሰርቶ ላወጣው ህዝብ ራሱን ለመግለጽ በፈለገ ጊዜ በነጎድጓድ ድምጽ ነበረ መገኘቱን ያበሰረው። እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን በትዳራችን ውስጥ እግዚብሔር እንዳለ የምናውቅበት አንደኛው መንገድ የእግዚአብሔር ድምጽ መሆኑን ነው። ይህ ድምጽ





የትዳራችን ህይወት ነው። ይህ ድምጽ ትዳርን ያስጀመረን ድምጽ እንደመሆኑ መጠን የሚያስጨርሰም ድምጽ ነው።

ይህ ድምጽ ቤታችን በችግር ውስጥ ሲያልፍ ወጀብና ማእበሉን ጸጥ የሚያደርግ ፍጥረት ሁሉ የሚታዘዝለት ድምጽ ነው። የተገነዘው ከነመግነዙ ከመቃብር እንዲወጣ ያደረገ ሙታን እንኳን የሚሰሙት ድምጽ ነው። ለሞተው ትዳር የሚያስፈልገው ከሰማይ የሆነ የትንሳኤ ድምጽ ነው። አልአዛር ሆይ ውጣ ብሎ የጠራው ድምጽ ነው።

ይህ ድምጽ ከውድቀት የሚያወጣና እንዳንወድቅም የሚጠብቅ ድምጽ ነው። በቤተክርስትያናችን ውስጥ ለሚጋቡት ተጋቢዎች የመጀመሪያ ምክሬና ትምህርቴ ስለ ትዳር ያለውን ዘዴና ጥበብ ወይንም መመሪያና መምሪያ መስጠት አይደለም። የመጀመሪያ ምክሬ የእግዚአብሔርን ድምጽ ለመስማት አብ ራችሁ ጸልዩ ነው። አብሮ የሚጸልይ ቤተሰብ ብቻ ነው አብሮ የሚኖረው። ጸሎት ህይወት ነው እንጂ በቤታችን ለተነሳው እሳት ማጥፊያ የእሳት አደጋ አይደለም። ጸሎት ከእግዚ አብሔር ጋር የመኖር የህይወት ዘይቤ ነውና።

ባሬ በውጪው አለምና በአገራችንም ቢሆን የተጋቢዎች ትልቁ ችግር አብሮ ያለመጸለይ ነው። ጸሎት ለትዳራችን እንደ አማራጭ ሳይሆን ከክርስቶስ ጋር የመኖር ግዴታችን ነው። ግዴታችን ከመኖራችን ጋር የተያያዘ ስለሆነ ነው እንጂ እግዚ አብሔር ስላስገደደን አይደለም። በህይወት ለመኖር መብላትና መጠጣት አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ግዴታችን ነው። ልክ እን ደዚሁም ሁሉ የማይጸልይ ቤተሰብ ከጊዜ በኋላ ትዳሩን ወደ ሞት ወይንም ወደ መለያየት ማድረሱ የማይቀር ነው።

ትዳርን ሰናሰብ አብሮ መጸለይን ማሰብ ግዴታ ነው። አብሮ ለመኖር አብሮ መጸለይ አስፈላጊ ነው። ይሀም አብሮ ለመጸለይ የምናደርገው መሰጠት መንፈሳዊ ፍቺ እንዳይኖር

ያግዳል። ስለዚህም በጸሎት መያያዝ ለመጸለይ ጊዜ መፍጠርና ትክክለኛ የጸሎት ጊዜን መወሰን ግድ ነው።

እግዚአብሔር አምላክ ራሱን ለአዳምና ሄዋን ይገልጥበት የነበረው ሁለተኛው መንገድ በኤደን ገነት መካከል ተክሎአት የነበረችው ዛፍ ናት። ይህችን ዛፍ እግዚአብሔር ያስቀመጠበት ምክንያት አለው። አዳምና ሄዋን ተቀብለውት የነበረው ስልጣን ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ ለስልጣናቸው የማይገዛ ፍጥረት አልነበረም። እግዚአብሔር አምላክ ደግሞ የማይታይ አምላክ ስለሆነ አምላክና ፈጣሪ እንዳላቸው ማሳያው መንገድ ይህች ዛፍ ነበረች።

አዳምና ሄዋን አምላካቸውን በሥጋ አይናቸው ማየት ባይችሉም መኖሩንና ስልጣኑን የሚያዩት በዚህች ዛፍ ነበር። ይህችን ዛፍ ባዩአት ጊዜ ሁሉ እግዚአሔር ያላቸውን ቃልና አምላካቸውን ያስታውሳሉ። ስለዚህ ነው ሰይጣን ስለ ዛፊቱ በተናገራት ጊዜ ሄዋን በዘፍጥረት 3፥3 «*እግዚአብሔር አለ ፤ እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ ፤ አትንኩም።*» አለን ብላ ለሰይጣን መልስ የሰጠችው። ከዚህም በላይ ይህች ዛፍ የተተከለችው በኤደን ገነት መካከል ነበር።

ይህ የእግዚአብሔር አሰራር ዛሬም አልተለወጠም። ይህም በሁለት ተጋቢዎች መካከል ላይ ጌታ የተክለው የእግዚ አብሔርን ቃል ነው። ሰው እናትና አባቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይጣበቃል ሲል ሁለቱም ተጋቢዎች ከእናትና አባታቸው ስልጣን ስር ወጥተው ወደ ግል ህይወታቸው ነጻነትና ህይወትን በራሳቸው ወደ መምራት ትልቅ ሃላፊነት ይገባሉ።

ይህ የሚያስደስትና ታላቅ በረከት ሆኖ ሳለ ከወላጆቻቸው ስልጣንና ቁጥጥር ስር የወጡት ተጋቢዎች ወደ እግዚአብሔር ቃልና መመሪያ ውስጥ በመግባት ለቃሉ እውቅና ሰጥተው በራሳቸው መኖር ካልጀመሩ የቤታቸው ራስና ገዢ እኔነት ይሆ





ንና ትዳራቸውን ለሥጋዊነት ወይንም ሳያውቁት ለሰይጣን አሰራር አሳልፈው ይሰጣሉ።

የቤታቸውም ችግር የሚጀምረው በዚህ ጊዜ ነው። ባለትዳሮች ላይ የማይታየው እግዚአብሔር ምሪትን የሚሰጣቸውና የሚያስተዳድራቸው በቃሉ ነው። የእግዚአብሔር ቃል የሚለውን ነገር እስካደረጉ ድርስ ብቻ ሁሉ ነገር ይገዛል። የኤደንን በረከት ያለምንም ፍርሃት መብላት ይጀምራሉ።

ልክ ለአዳምና ሄዋን ከዚህች ዛፍ በበላችሁ ቀን ሞትን ትሞታላችሁ እንደተባለ የእኛም ጋብቻ የሞተ የሚሆነው ገንዘብ ስለሌለ ልጅ ስለሌለ የተለያዩ ነገሮች ስለሌሉ ሳይሆን የእግዚ አብሔር ቃል ሉአላዊነት ከቤታችን ሲርቅና ለቃሉ መታዘዝ ስናቆም ብቻ ነው።

አዳምና ሄዋን ያችን ዛፍ ፍሬዋን በበሉ ጊዜ ወዲያውኑ መፍራት ጀመሩ። ራቁታቸውን እንደሆኑ ስላወቁም የራሳቸውን ቅጠል ሰፍተው ለበሱ። ከሁሉም በላይ በመካከላቸው የነበረው ፍጹም አንድነት ተለውጦ የክስ ቤት ሆነ።

የትዳር ችግር የሚያጋጥመን ችግር ሳይሆን የእግዚ አብሔር ቃል መጣስ ነው። ለእግዚአብሔር ቃል ያለን ክብርና መታዘዝ ሲቀንስ እርስ በርስ ያለው መከባበርና መዋደድ ይቀን ሳል። ቃሉን ባከበርነው መጠን ያከብረናል። በናቅነው መጠን ተሰበቀስ ወዳላሰብነውና ወዳልጠበቅነው ውድቀት እንሄዳለን።

## *3. የጸጋ ልብስ*

በፍጥረት 2፥25 «*አዳምና ሚስቱ ሁለቱም እራቁታቸውን ነበሩ አይተፋፈሩም ነበር።*» ከላይ እንዳየነው ለአዳምና ሄዋን ጋብቻ መቃናት ሁለቱ ምክንያቶች ከአምላካቸው ጋር ያለው ግንኙነት ነበር። ይህም በመገኘቱና በቃሉ ስልጣን ስር መኖር

ነው። ይህ ሦስተኛው ግን በተጋቢዎቹ መካከል ስላለው ግን ኙነት መሰረታዊ የሆነ መልእክት ያለውን ነገር ያስተላልፋል።

በምድር ላይ ላለን ኑሮ እግዚአብሔር በሰጠው መመ ሪያዎች ሁሉ በቅድሚያ ከእርሱ ጋር ስላለን ህብረትና አንድነት እንዴት መኖር እንዳለብን ካስገነዘበ በኋላ በሰዎች መካከል እርስ በእርስ እንዴት መኖር እንዳለባቸው ያሳስባል።

ለምሳሌ በዘጸአት 20 ላይ እግዚአብሔር ለእስራኤል ህዝብ ለመጀመሪያ ጊዜ በሙሴ አማካኝነት እንዴት መኖር እን ዳለባቻው የሚያሳየውን አስርቱን ትእዛዝ ሲሰጥ ከአስሩ ውስጥ የመጀመሪያዎቹ አራቱ ትእዛዞች ከአምላካቸው ጋር እን ዴት መኖር እንዳለባቸው የሚያሳዩ ሲሆን ቀሪዎቹ ስድስቱ ትእዛዞች ደግሞ ከሰዎች ጋር እንዴት መኖር እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው።

1ኛ/ ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኑሩህ
2ኛ/ የማንኛውንም ምሳሌ የተቀረጸውን ምስል ለአንተ አታ ድርግ
3ኛ/ የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ
4ኛ/ ሰንበትን ቀድሰው
5ኛ/ አባትና እናትህን አክብር
6ኛ/ አትግደል
7ኛ/ አታመንዝር
8ኛ/ አትስረቅ
9ኛ/ በባልንጀራህ ላይ በሃሰት አትመስክር
10ኛ/ የባልንጀራህን ቤት ሚስት ሎሌውን ገረዱንም በሬውንና አህያውን እንዲሁም ገንዘቡን አትመኝ።

በትዳር ውስጥም ያለው ህብረትና አንድነት ተመሳሳይ ነው። አስቀድሞ በእግዚአብሔር መገኘትና በእግዚአብሔር ቃል ስልጣን ስር መኖር እንዳለባቸው ከተናገረ በኋላ በመጨረሻ





እርስ በርስ እንዴት መኖር እንዳለባቸው ሲያሳይ እራቁታቸውን እንደ ነበሩ ነገር ግን እንደማይተፋፈሩ በመግለጽ የትዳራቸውን ሚስጢር በግልጽ አሳይቶአል።

በመጽሃፍ ቅዱስ ላይ ራቁትነት ምን እንደሆነና መልበስ ወይንም ራቁት አለመሆን ምን እንደሆነ በብዙ መልኩ ተገልጾአል። ራቁትነት የሃጢአት ፣ የውድቀት ፣ የውርደትና ጸጋን የማጣት ምልክት ነው። በራእይ 3፥17 ሃብታም ነኝ አን ድስ እንኳን አያስፈልገኝም ትል ለነበረችው የሎዶቅያ ቤተክርስትያን ጌታ *«ደሃ እውርም ፣ የተራቆትህም መሆንህን ስለማታውቅ ፤ ባለ ጠጋ እንድትሆን በእሳት የነጠረውን ወርቅ ፤ ተንናጸፊህም የራቁትነትህ ሃፍረት እንዳይገለጥ ነጭ ልብስን ፤ እንድታይም አይኖችሽን የምትኳለውን ኩል ከእኔ ትገዛ ዘንድ እመክርሃለሁ»* በማለት መንፈሳዊ መራቆትዋን በስጋዊ መራቆት መስሎ ገልጸት አናያለን።

ምንም እንኳን መጽሀፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር ፊት በራሳችን የበቃን ልንሆን እንደማንችል ቢነግረንም ነገር ግን ክርስቶስን እንደ ልብስ ልበሱት በማለት ፍጹም ጻዲቅና ቅዱስ በሆነው አምላካችን ፊት ያለ እንዳች ፍርሃት እንድንቆም ያደረገንን የጸጋ ልብስ ኢየሱስ እንደሆነ ይነግረናል።

አዳምና ሄዋን ሃጢአት ከመስራታቸው በፊት ራቁታቸውን ነበሩ። ይሁን እንጂ ፊጽሞ አይተፋፈሩም ነበር። ይህም ራቁ ትነታቸውን የሸፈነ የማይታይ ልብስ በመኖሩ ነበር ወይንም ራቁታቸውን እንዳይተያዩ የሚያደርግ ሃይል ነበር።

እኛን በእግዚአብሔር ፊት ራቁታችንን እንዳንታይ ያደረ ገን ታላቁ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው። ጌታ ኢየሱስ ወደ ምድር ሲመጣ ለብሶ የመጣው ልብስ ጸጋንና እውነትን ነው። በእኛና በእግዚአብሔር መካከልም ለዘለአለም ለብሰን የምንኖረው

ልብስ ቢኖር የጸጋ ልብስ ነው። መቼውንም ቢሆን በፊቱ በቅተን ልንኖር ስለማንችል የበላለየ ልብሳችንን በክርስቶስ አለበስን። ስለዚህ ሁልጊዜ በፊቱ ያለ ፍርሃት በነጻነት እን ኖራለን።

ይህ የጸጋ ልብስ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ብቻ ያለ ሳይሆን በሰውና በሰውም መካከል ያለ ልብስ ነው። የትዳር ቀውስ የሚጀምረው ይህ የጸጋ ልብስ ከተጋቢዎች አይን ላይ ሲወሰድ ነው። አዳምና ሄዋን ራቁታቸውን ነበሩ። ነገር ግን አይተፋፈሩም ነበር። ምክንያቱም አንዱ የሌላውን ጉድለት የሚያይበት አይን ስላልነበራቸው ነው።

ብዙ ተጋቢዎች በእጮኝነታቸው ጊዜና በጋብቻቸው የመ ጀመሪያ አመታት ውስጥ ሰላም የሞላበትና የመከባበር ኑሮ ይኖራሉ። ይህም በትዳራቸው ውስጥ ሁለቱም ተጋቢዎች ያለ ስህተት እየኖሩ ነበር ማለት ሳይሆን ስህተትን ወይንም በእያን ዳዳቸው ውስጥ ያለውን ድካም ለማየት እንዳይችሉ የጸጋ አይን ስለ ነበራቸው ነው። እየቆየ ሲመጣ ግን ሳያውቁት ይህ ንን ጸጋ ያስወስዱታል። ያን ጊዜ ትንሽዋ ችግር ትልቅ ትሆናለች። ቀድሞ ችግር መስሎ የማይታየው ነገር ሁሉ አሁን በማጉያ መነጽር የታየ ያህል ትልቅና ከባድ ችግር ሆኖ ይታያል። ይህም በጋብቻቸው ምርጫ ላይ ስህተት እንደሰሩ እስኪያስመስል ድረስ የጸጸትና የሃዘን ኑሮ እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል።

እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የጸጋ አይን ማየት ቀርቶ እግዚአብሔር እኛን ያየበትን የጸጋ አይን ለመቀበል አንችገራ ለን። ጸጋ የነጻ ስጦታ እንጂ ደሞዝ አይደለም። ባለቤቴን የምወዳት ስላደረገችልኝ ወይንም ስለምታደርግልኝ ነገር ሳይሆን ማንነትዋን እንዲሁ በመቀበል በነጻ የምሰጠው ፍቅር እሱ የጸጋ ፍቅር ነው። ከጥቅምና ከምታደርግልኝ ነገር ጋር የተያያዘ ከሆነ





ግን ይህ ከጸጋ የወደቀ የኋላ ኋላ ትዳሩን አደጋ ላይ የሚጥል ነው።

ከጥቂት አመታት በፊት ወደ አንድ ቤተሰብ ከባለቤቴ ጋር ሄደን ነበር። የሄድንባቸው ቤተሰብ ባለቤት የሚታይ ችግር ያለውና ለመኖር አስቸጋሪ የሆነ ባህሪይ እንዳለው ለመገመት የማያስቸግር ነበር። ይሁን እንጂ ባለቤቱ ያስደነቀኝን ነገር ስትናገር ሰማሁ። ይህች ሴት ብዙ ሰው ባለቤቷን ስለ ማይረዳት ይፈርዱበታል ፤ ቢያውቁት ግን በጣም ጥሩ ሰው ነው አለችን።

ይህች ሴት ስለ ባለቤትዋ ያላትን አስተያየት ስትሰጥ ፣ የእግዚአብሔር ጸጋ ይህንን እኛ እንኳን ከውጪ አይተን ለመቅረብ የተቸገርነውን ሰው እስዋ ግን በጸጋ አይንዋ ታውሮ በፍቅር አብራው ለመኖር በመቻልዋ ተደንቀን ታላቅ ትምህርት ተምረን ወጣን።

በርግጥ የትዳር ችግር ችግሩ አይደለም ፤ ችግሩ በአብ ባኛው ቀድሞውንም ከጅምሩ ነበር። የተለወጠው ነገር ቢኖር ግን ለባ ሰው ያለንን አይታ ነው። ቀድሞ በጸጋ አይን ስላየነው ስህተቱን የምናይበት አይን አልነበረንም። አሁን ግን ጸጋው ሲወሰድ ራቁቱን እንደሆነ ሰው ሆኖ ያንን ሰው ለመቀበል እን ቸገራለን።

ለመሆኑ ችግር የሌለው ሰው ማን ነው? ስህተትንስ የማያደርግ ሰው ማን ነው? አይነቱና ቀለሙ ይለያይ እንጂ ሁሉ ሰው የራሱ የሆነ ድካምና ችግር አለው። ቤታችን ጭቅጭቅ ካለው ጸጋ ጎሎአል ማለት ነው። የጸጋ ሁሉ አምላክ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ጸጋችንን እንዲመልስ ብንጸልይ ችግሩ ሳይሆን እኛ እንለወጣለን። ያም ለቤታችን ትልቅ ፈውስና በረከትን ያመጣልናል።

፭

# የትዳር ውድቀት ጅማሬ

የትዳር ትልቁ አላማ ሰው አምላኩን መስሎ በአንድነት ከዘላለም እስከዘላለም ስለ እግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር ምድርን እየገዛ እንዲኖር ነበር። ይህንን አላማውን በሳተ ጊዜ ግን ሰው ለሚገዛው ነገር ተገዛ። ለእርሱ የተፈጠረው ነገር ሁሉ በእርሱ ላይ ተነሳበት። ምድር እንኳን እሾህንና አሜከላን አበቀለችበት። ሌላው ቀርቶ ሰው እርስ በርሱ እንዳይስማማ መካሰስ ጀመረ። ከዚህም በላይ ስለ ራሱ የነበረው አመለካከት ተለውጦ የራሱን ሰውነት በሃፍረት ቅጠልን ማገልደም ጀመረ።

ለመሆኑ የአዳምንና የሄዋንን ትዳር ከዛ የሥልጣንና የክብር ኑሮ ምን አወረደው? ለብዙ ሰው አጭሩ መልስ እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ ያችን ፍሬ ስለበላ ነው የሚል ይሆናል። ይህ በርግጥ ትክክለኛ መልስ ነው። ይሁን እንጂ ያችን ፍሬ እንዲበሉ ምን አደረጋቸው? ብለን መጠየቅ ይኖርብናል። ለዚህም ሰይጣን አሳስቶአቸው ነዋ የሚል መልስ ለመስጠት ይቻላል። ይሁን እንጂ ከዚህም በፊት ሊታይ የሚገባ አንድ መሰረታዊ ነገር ልንመለከት ይገባናል።

እግዚአብሔር የአዳምና ሄዋንን ትዳርና ኑሮ ሲመሰርት ሁለቱ አንድ እንዲሆኑ ነበር። ይህም ማለት በውሳኔአቸው ልክ እንደ እግዚአብሔር ተመካክረው አንድን ውሳኔ እንዲወስኑ ፣ በሚሰሩት ሥራም ተመካክረው አንድን ሥራ እንዲሰሩ ነበር። ይህንን ከራሱ ከእግዚአብሔር አሰራር ላይ ማየት እንችላለን።

እግዚአብሔር አምላክ ሰውን ሲፈጥርም ሆነ ማንኛውንም ሥራ ሲሰራ በምክር ነው። ሰውን በምሳሌአችን እንደ አምሳላችን እንፍጠር ብሎ ሲፈጥረው በውሳኔው ላይ የአብን ወይንም የወልድን ተሳትፎ ብቻ ሳይሆን አብ ፣ ወልድ ፣ መንፈስ ቅዱስ የተሳተፉበትን ሥራ በአንድነት ሰርተዋል።

በኤፌሶን አንድ ላይ እግዚአብሔር ለውን ሊያደን ባወጣው እቅዱ ላይ ከራሱ ጋር ተማክረና ከምክሩ በኋላ ፈቀደ ፣ በፈቃዱም መሰረት ሥራውን ሰራ። ለውም ይህንን አሰራር ተከትሎ እንዲሰራ አንድ ሆኖ ነበር።

ነገር ግን አንድ ቀን ሰይጣን ሄዋን ብቻዋን በነበረችበት ጊዜ መጣ። ለመሆኑ ለይጣን ለምን በአንድ ላይ ሳሉ አልመጣም? ብቻዋን ለምን ፈለጋት? በርግጥ ችግሩ ሄዋን ብቻ ዋን መሆንዋ አልነበረም። ችግሩ ሰይጣንን ማዋራትዋም አልነበረም። ምክንያቱም ሰይጣን ዛሬ የምናውቀውን አይነት ሥልጣን ያኔ አልነበረውም። እንደውም ለሰው ሥልጣን የሚገዛ የሰው ተገዢ ነበር። ሰይጣን ሄዋንን አሳታት እንጂ እንደ ባለስልጣን አላስገደዳትም። ሄዋን ስልጣንዋን ተጠቅማ ሂድ ብትለው በርግጥ ታዞ ይሄድ ነበር።

ስለዚህ ነው ሰይጣን በማስገደድ ሳይሆን በጥያቄ ወደ ሄዋን የመጣው። አላማው ከእግዚአብሔር ለመለየት ብቻ ሳይሆን ለሰው የነበረውን ሥልጣን ለመውሰድ ጭምር ነበር። የሰው ሥልጣኑ ምንጭም እግዚአብሔርን መምሰሉ ነበርና።





ታድያ ሰይጣን እንዴት ተሳካለት? ትልቁ ስህተት ሄዋን ከአዳም ሳትማከር ውሳኔዋን በራስዋ መወሰንዋ ነበር። ያ የተፈጠሩበትን እግዚአብሔርንም እንዲመስሉ የተሰሩበትን ትልቅ አላማና ሃሳብ ጣሰች።

እዚህ ላይ ነው የሰው ልጅ ውድቀት የጀመረው። ሰው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሲጥስ ዛፉቱን መብላቱ ብቻ ሳይሆን የተፈጠረበትን አላማ መርሳቱ ነበር። ምን አልባት ሄዋን ሰይጣን በፈተናት ጊዜ አዳምን አማክራ ቢሆን ኖሮ ውጤቱ ምን ሊሆን ይችል ነበር? ይህንን አሰበው ያውቃሉ? ምንም እን ኳን ትክክለኛው መልስ ይሄ ነው ብለን ባንከራከርም ሄዋን አዳምን አማክራው ቢሆን ኖሮ ያችን ፍሬ ባልበሉ ነበር ብለን ለማለት እንችላለን።

የሰውን ልጅ ውድቀት ጅማሬ ከብዙ አንጻር ማየት ቢቻልም ለዚህ የጋብቻ ሃሳብ ግን በቂ ትምህርት ያለውን ይህ ንን የትዳርን ትልቅ አላማ ጥሶ የመጀመሪያውን ትዳር የጣለ ፣ የተጣሰውን የአንድነት ህግ መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች ያሉትን ሃሳቦች አነሳለሁ።

የሄዋን ህብረት ከእግዚአብሔርና ከአዳም ጋር ነበር። የህብረትዋም ምንጭ አንድነትዋ ነበር። የሥልጣንዋም ምንጭ ከእግዚአብሔርና ከአዳም ጋር ያላት ህብረትና አንድነት ነበር። እነዚህ ሁለቱ ሊነጣጠሉ የማይችሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው። የጋብቻም ሆነ የሰው ህይወት መሰረቱ በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ከዛም ከሰው ጋር ባለው ህብረት ላይ ይመሰረታል። እግዚአብሔርን ይዞ ሰውን መርሳት አይቻልም። ሰውን ይዞ እግዚአብሔርን መርሳት አይቻልም።

ይህንን ክፍል ልብ ብለን ካየን ሄዋን እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር ፈጽሞ አልረሳችም። ይህ ብቻ ሳይሆን

የምትወስደው እርምጃ ሞት ሊያመጣ እንደሚችል አልዘነጋችም። ከሰይጣን ለቀረበላትም ጥያቄዎች ሁሉ ትክክለኛውን መልስ እንዲህ ብላ ነበር የሰጠችው። *«እግዚአብሔር አምላክም አለ ከዚች ዛፍ እንዳትበሉ በበላችሁ ቀን ሞትን ትሞታላችሁ።»*

ሃዋርያው ጳውሎስ ስለ ሰው ውድቀት ሲናገር መነሻው የሄዋን መታለል ነው ይላል። ታድያ ሄዋን ለቀረበላት ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ ከሰጠች ፣ የአምላክዋን ቃል ሳትረሳ የሚያመጣውንም ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል እያወቀች እንዴት ታለለች? እንዴትስ ሳተች? ስህተት ወይንም መታለል ታድያ ከየት ይጀምራል? መነሻውስ ምንድን ነው?

**«እግዚአሐርን ይዞ ሰውን መርሳት አይቻልም። ሰውን ይዞ እግዚአብሔርን መርሳት አይቻልም።»**

ሰይጣን ሄዋንን ለማሳትና ለመጣል ሦስት መስታዊ ደረጃዎችን ተጠቅሞአል። እነዚህም ሦስት ነገሮች እስከዛሬ ድረስ ሰውን ከእግዚአብሔርና ሰውን ከሰው ለመለየት ሲፈልግ የሚጠቀምባቸው መሳሪያዎች ናቸው። እነዚህም አንደኛ ሃሰብ ፣ ሁለተኛ እኔነትና ሦስተኛ የግል ውሳኔ ናቸው። እነዚህ በጣም ቀለል የሚመስሉ በውስጣቸው ግን ታላቅ ሃይል ያላቸው የጠላት መሳሪያዎች ናቸው። ለማስረዳት እንዲረዳኝ ግን ከታች ወደ ላይ ዘርዝሬ አቀርባቸዋለሁ።

## *የግል ውሳኔ*

የሄዋን መውደቅ ሚስጢር ልብዋንና ሃሳብዋን ከእግዚአብሔርና ከአዳም ላይ አንስቶ ወደ ራስዋ ወስዶ በውስጥዋ





ያለውን የግል ፍላጎትዋን አነሳስቶ በግልዋ ያለ ባልዋ ምክር መወሰንዋ ነበር። ከትዳር በፊት ለብቻው እንደወደደ ሲወስን የኖረ ሰው ወደ ትዳር አለም ሲገባ ማስተዋል ያለበት ነገር ቢኖር ከዚህ በኋላ በግሉ ምንም ነገር መወሰን እንደሌለበት ነው።

ሁለቱ አንድ ሆነዋልና ሁለቱ በአንድነት ሊወስኑ ይገባል። ይህ ለብዙ ሰው በትዳር መታሰር ይመስለዋል። ነገር ግን ከሄዋን እንደምንረዳው ከውድቀት የመጠበቂያው መንገድ እንጂ መታሰሪያው አይደለም። ታድያ ሄዋንን ይህንን የግል ውሳኔ እን ድትወስን ምን ገፋፋት? ብለን መጠየቅ ይኖርብናል። መልሱ በውስጥዋ የተነሳው ፍላጎት ወይንም ምኞት ነበር።

ዘፍጥረት 3፥6 ላይ ቤቲቱም *«ዛፉ ለመብላት ያማረ እን ደሆነ ለአይንም እንደሚያስጎመጅ ለጥበብም መልካም እንደሆነ አየች»* ይላል። ለማስመርና ለመከተል የፈለኩት ቃል ያማረ የሚለውን ቃል ነው። ቃሉ በእንግሊዘኛው ትርጉም ላይ (desirable) ይለዋል።

ሰይጣን ሄዋንን ያናገራት በልብዋ ያንን አምሮት እስከት ከትለት ድረስ ብቻ ነው። ልክ አምሮቱን ከከተተ በኋላ ሄዋንን ይመራት የነበረው ሰይጣን ሳይሆን አምሮትዋ ነበረ። ከፍሬው ወስደች በላች ለባልዋም ሰጠችው።

ያዕቆብ 1፥14 *«እግዚአብሔር ማንንም በክፉ አይፈትንም ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል። ከዚህ በኋላ ምኞት ጸንሳ ሃጢአትን ትወልዳለች ሃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች።»*

የሰው ውድቀት ወይንም የመነሳቱ ጅማሬ ምኞቱ ነው። ምኞት መልካም የሆነ ከእግዚአብሔር የሚሰጠን አለ ፣ መል

ክም ያልሆነ በራስ ላይ ያማከለ ምኞት ደግሞ አለ። ትክክለኛው ምኞት ከእግዚአብሔር ቃልና ከመንፈሱ ለይተን ካላወቅንና በትክክለኛው መንገድ ካልመራነው በቀር የሰው ምኞት ልጓም እንደማይዘው እንደ በረገገ ፈረስ ይሆናል።

በትዳር ውስጥ እንደ ከገባን በኋላ ያማረንን ሁሉ የምን በለበት ዘመን አብቅቶአል። ትዳር የራስ ፍላጎታችንንና አምሮታችንን የምንገታበትና ለጌታና ለትዳር ጓደኛችን የምን ኖርበት ቦታ ነው። የሰይጣን ትልቁ ፕላን የሄዋንን ፍላጎት ከእግዚአብሔርና ከባልዋ ላይ አንስቶ ወደ ራስዋ ማድረግ ነበር። ይህ ፍላጎትዋ በተነሳ ጊዜ ማንኛውንም የምታውቀውን የእውነት ቃልም ሆነ የፍርድ ቃል ጥሳ በራስዋ ውሳኔ እንድትን ቀሳቀስና ዛፉትዋን እንድትበላ አድርጓታል።

ምኞት ሃይለኛ ነገር ነው። ምኞት ሰው ህይወትን ሲጀምር የሚለማመደው የመጀመሪያ ነገር ሲሆን ከመሞቱም በፊት የሚጥለው የመጨረሻ ነገር ቢኖር ምኞት ነው። በመክብብ መጽሃፍ ምእራፍ 12፥5 ላይ የሰው ህይወት ከጎልማሰነቱ ጀምሮ እስከ ሞቱ ድረስ ምን እንደሚመስል ጠቢቡ ሰለሞን ከገለጸ በኋላ «*ፈቃድ ሲጠፋ ሰውም ወደ ዘላለም ቤት ሲሄድ*» ብሎ ሰው ከመሞቱ በፊት በመጨረሻ የሚጥለው ነገር ፈቃዱ እን ደሆነ ይናገራል። ይህ የአማርኛው ትርጉም ፈቃድ የሚለውን ቃል የእንግሊዘኛው ምኞት ወይንም ፍላጎት ይለዋል።

በሚክያስ 2፥1 «*በመኝታቸው ላይ በደልን ለሚያስቡ ክፋትንም ለሚያደርጉ ወየውላቸው ፤ ሃይል በእጃቸው ነውና ሲነጋ ይፈጽሙታል።*» ሰው በልቡ ውስጥ አንድ ጊዜ በምኞት ከረገዘ ያረገዘውን ሳይወልድ አያቆምም። በዚህ ክፍልም ላይ ሃይል በእጁ ነውና ሲል የሰው ሃይሉ ያለው በምኞቱ ውስጥ እንደሆነ ሲያስገነዝብ ነው።





በህይወት ላይ የምንመኘው ነገር መኖሩ ተገቢ ነው። ይሁን እንጂ ያንን በውስጣችን ያለውን ምኞት መመርመርና ማስመርመር የእግዚአብሔር ሰው ባህሪይ ነው። ከጥቂት አመ ታት በፊት በእግዚአብሔር ለመጋቢነት አገልግሎት ወደ ሚኔ ሶታ ተጠራሁ። ምንም እንኳን ለብዙ አመት የጸለይኩበት የጸሎት መልስ ቢሆንም ሰይጣን የሰውን ህይወት በር በመዝጋት ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ያልሆነን በር በመክፈት እንደሚዋጋ ስለማውቅ ይህ ጥሪ ከእግዚአብሔር መሆኑንና አለመሆኑን ለመጠየቅ ወደ ጌታ አጥብቄ አጸልይ ነበር።

አንድ ቀን ምሽቱን ሁሉ ለረጅም ሰአት ሰጸልይ ድንገት የጌታ ድምጽ ልጠራጠረው በማልችለው መልኩ ወደ ሚኔሶታ መሄድ እንዳለብኝ በቃሉ ደግፎ ተናገረኝ። ይህ ድምጽ ግልጽና የማያሻማ ነበር። ይህንን ድምጽ እንደሰማሁ መጀመሪያ ወደ አእምሮዬ የመጣችው ባለቤቴ ነበረች።

ድምጹ በትክክል ከጌታ ነበር። ይሁን እንጂ ባለ ትዳር ስለሆንኩ ጌታ ተናገረኝ ብዬ ዘልዬ ወደ ውሳኔ መሄድ አል ፈለኩም። እንደውም ይህ ጉዳይ ከጌታ ከሆነ ሊሰማማ የሚ ገባው የመጀመሪያ ሰው ቢኖር ባለቤቴ መሆንዋን ተገነዘብኩ። ወዲያው በነጋታው ባለቤቴን ጠርቼ ስለ ሁኔታው ከነገርኩዋት በኋላ እንዲህ አልኳት፦ «እኔ ከጌታ የሆነውን ሰምቼ ጨርሻለሁ። ይህ ድምጽ ከጌታ መሆኑንና አለመሆኑን አንቺ ደግሞ በተራሽ ፈትኚው። ከተስማማሽ እንሄዳለን ካልተስማማሽ ግን ወይ እስክትስማሚ እጠብቃለሁ አለዚያም ይቀራል» አልኩዋት።

የሚያስገርመው ነገር አስራ አምስት ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ባለቤቴ ይህ ነገር ከጌታ ነውና መሄድ አለብን አለች። እንደውም ለመሄድ ያሰብኩት በጁን ወር 1995 የነበረውን ጌታ ከተናገረ ምን መቆየት ያስፈልጋል በማለት በፌብሩዋሪ ወር

በሜኔሶታ የብርዳማ ወቅት ተነስተን ወደ ሚኔሶታ ገባን። ጌታም እንደተናገረው በሀች ምድር ባረከን።

ብዙ ሰው ጌታ ነው የተናገረኝ ይህ በልቤ ያለ ከልጅነት ጀምሮ ላደርግ ያሰብኩት ነገር ነው ወዘተ... በማለት ካገባ በኋላ ከትዳር ጓደኛው ሳይማከርና ሳይስማማ በራሱ መንገድ ይጀምራል። በዚህ ምክንያት ሰይጣን በተጋቢዎቹ መካከል የልብ መራራቅና አለመተማመን በመፍጠር መለያየትን ያመጣል።

አንዳንድ ሰው ይህንን ሃሳብ ሲሰማ ባለቤቴ ጌታን እያ ውቅም ወይንም አታውቅም እንዴት በመንፈሳዊ ነገር ልንስማማ እንችላለን? የሚል ጥያቄ ያነሳል። ለዚህ ያለኝ መልስ ጌታ ለሚያምኑት ብቻ ሳይሆን ለማያምኑት ሁሉ ይናገራል። እን ደውም ከመጽሃፍ ቅዱስ እንደምናየው ቂሮስ የተባለውን ንጉሥ የጌታን ሥራ እንዲሰራ እንደቀባው ይናገራል።

ጥያቄው ባለቤቴ ሊሰማማ ወይንም ልትስማማ ትችላለች ወይ? ሳይሆን ጌታ ተናገረኝ በምንለው ነገር ላይ ምን ያህል ጌታ እንደተናገረን እርግጠኞች ነን? ነው። ጌታ ከሆነ የተ ናገረውን እንዲፈጽም የሚተጋና የታመነ ነውና በትእግስት እን ጠብቅ።

መልእክቴ አንድ ነው። ትዳር ሊፈርስ ሲጀምር የመጀ መሪያው የሰይጣን ሥራ በተጋቢዎቹ ውስጥ የሬሳቸው የሆነ ከትዳር ጓደኛቸው የተለየ የግል ፈቃድና ምኞት በመዝራት ሳይስማሙ በግል ውሳኔ እንዲወስኑ ማድረግ ነው። ወንድሜና እህቴ ሆይ ዛሬ ከትዳር ጓደኛችሁ ውጪ በግላችሁ አይታችሁ ያማራችሁ ዛፍ ምን ይሆን? ያ ለመጥፊያ ከሰይጣን የተዘጋጀ ወጥመድ ነውና እንጠንቀቅ። ያንተ ምኞት የሚስትህም ምኞት ሊሆን ይገባል። ወይንም ሚስትህ አይታ የምታምንበት ምኞት ሊሆን ይገባል። ያን ጊዜ ከክፉ ትጠበቃለህ።





***እኔነት***

ሰይጣን ሄዋንን ለማሳት የተጠቀመበት መንገድ አንዱ ወደ ራስዋ ብቻ እንድትመለከት በማድረግ ነው። በዚያን ሰአት ሄዋን የታያት የዛፉ ማማር ማስ ጎምጀቱና ልታገኘው የምትችለውን ጥቅም ከራስዋ ጋር በተገናኘ መልኩ ብቻ እንጂ ስለ አዳም ምንም ግድ አልነበራትም። ሄዋን አዳምን አትወደም ነበር ማለት አልነበረም። እግዚ አብሔርንም አትፈራም ነበር ማለት አይደለም። ነገር ግን ሰው በራሱ ምኞት ሲዋጥ በእኔነት እስር ቤት ውስጥ ይገባል። ይህም ሁሉንም ነገር ያሰረሳዋል።

**«ሰው በራሱ ምኞት ሲዋጥ በእኔነት እስር ቤት ውስጥ ይገባል። ይህም ሁሉንም ነገር ያሰረሳዋል።»**

ሰው አንድ ጊዜ በትዳር ከተሳሰረ በኋላ አንድ ነው እንጂ ሁለት አይደለም። የትዳር ዋና አላማ ሁለቱ በአንድ ቤት ተሰ ማምተው መኖራቸው ሳይሆን ሁለቱ አንድ መሆናቸው ነው። በቤተክርስትያናችን ውስጥ ለጋብቻ የሚዘጋጁትን ተጋቢዎች የጋብቻ ትምህርት በማስተምርበት ጊዜ ከምጠይቃቸው ጥያቄ መካከል አንዱ ሰው ለጋብቻ ደርሶአል የምንለው መቼ ነው? የሚል ነው። እንባቢዎቼንም ይህንን ጥያቄ መጠየቅ እፈ ልጋለሁ።

እዎን ሰው ለትዳር ተዘጋጀ የምንለው መቼ ነው? መልስዎ ለአቅመ አዳም ሲደርስ ፣ ትምህርቱን ሲጨርስና ትዳር ለመያዝ የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነገሮች ሲኖሩት ወዘተ... የሚል ሊሆን ይችላል። ልክ ነው ፤ እነዚህ ነገሮች ሁሉ ለትዳር አስፈላጊ ናቸው።

ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ እንዳሉ ሆነው አንድ ሰው ለአቅመ አዳም ከደረሰ በኋላ ራሱን ሊጠይቅ የሚገባው ትልቅ ጥያቄ ቢኖር ካገባሁ በኋላ የምኖረው ለራሴ ነው? ወይስ ለትዳር ጓደኛዬ? ይህ ጥያቄ መልስ እስካገኘ ድረስ ትዳር ክባድና አስፈሪ ቦታ ሳይሆን የበረከትና የማፍሪያ ቦታ ይሆናል።

ብዙ ሰው ትዳርን ሲያስብ ከትዳር ጓደኛው ስለሚያገኘው ጥቅም እንጂ ለትዳር ጓደኛው ሊያደርገው ስለሚችለው ነገር አስቦ ወደ ትዳር አለም ስለማይገባ ጥቂት እንደቆዩ ብዙ መጎዳት ብዙ ሃዘን ይገጥማቸዋል። የጠበቁትና የሚያገኙት ነገር ፈጽሞ የተለያየ ስለሚሆንባቸው «ትዳር እንዲህ ነው እንዴ? ለምን አገባሁ? እንዲህ መሆኑን ባውቅ አላገባም ነበር» ሲሉ ይሰማሉ።

ለማንኛውም ህብረትና ግንኙነት መሰረቱ ከእኔነት ወጥቶ ህብረት ለማደርገው ሰው ምን ቁም ነገር ማበርከት እችላለሁ የሚል መሆን ይገባዋል። ጌታ እየሱስ ወደ ምድር ከሰው ጋር ህብረት ለማድረግ በመጣ ጊዜ ከሰው ጋር ላለው ህብረት መሰረት ያደረገው ይህንን ሃሳብ ነበር። ለዚህም በብዙ ቦታዎች ላይ እንዲህ እያለ የመጣበትን አላማ ይናገር ነበር። «የሰው ልጅ እንዲያገለግል እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም"።»

በዮሃንስ ወንጌል 13፥13-14 *«እንግዲህ ጌታና መምህር ስሆን እኔ እግራችሁን ካጠብኩ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል።»* በማለት እርሱ ከእነርሱ ጋር ያለው ህብረት እነርሱን የማገልገል እንጂ በእነ ርሱ ለመገልገል እንዳልሆነ በመናገር ብቻ ሳይሆን በተግባር በማሳየት የእናንተም ህብረትና አንድነት መሰረቱ ሊሆን የሚ ገባው መገልገልን በመፈለግ ሳይሆን ማገልገል በመፈለግ መሆን ይገባዋል በማለት አስተምሮአቸዋል። ወርቃማው ቃል ተብሎ የሚጠራው ጥቅስ ላይ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን





ሁሉ እናንተም እንዲሁ አድርጉላቸው በማለት ጌታ እየሱስ ጨምሮ አስተምሮአል።

ጌታ በአምላክነቱ በእርግጥ ትልቅ ነው ፤ አምላክ ነው ፤ ጌታ ነው። ይሁን እንጂ ለደቀ መዛሙርቱ የትልቅነትን ትም ህርት የሰጠው በማገልገል ውስጥ ነው። ትልቅነት በመገልገል ሳይሆን በማገልገል ይጀምራል። ጥቅምን በማስጠበቅ ሳይሆን ጥቅምን በመጣል ይታያል።

አንድ ሰው ከእኔነት ሲወጣ ትልቅ ምልክቱ መንፈሱም ልቡም ሃሳቡም ወደ ማገልገል ይለውጣል። ለሰው ከእኔነት የበ ለጠ ትልቅ እስር ቤት የለውም። ብዙ ሰው በሥጋ ነጻነት ያለው ይምስል እንጂ የሚኖረው በእኔነት እስር ቤት ነው። አን ድ አገልጋይ አንድ ቀን እንዲህ ብሎ ተናገረ።

አንድ ጫጩት በእንቁላል ውስጥ እስካለች ድረስ የአርስዋ አለም የተወሰነው በምትነካውና በምትዳሰሰው የእን ቁላል ሽፋን ብቻ ነው። ልክ ግን ያንን ሽፋን ሰብራ ወይንም አስብራ ስትወጣ የምትገባበት አለም ግዙፍና በሀሊና ሊታሰብ የማይቻል ነው።

ከእኔነታችን ሽፋን ስንወጣ ወደማናውቀው ትልቅና ሰፊ አለም ውስጥ እንገባለን። ችሎታችንን ፤ ሃይላችንንና እውቀ ታችንን ለሌሎች ማዋል ስንጀምር ያን ጊዜ የመኖር ትርጉም እናገኛለን። ክብርንና ታዋቂነትን እናገኛለን። በአለም ላይ የሚደነቁ እኔም የማደንቃቸው ታላላቅ ሰዎች አሉ። ከእን ዚህም መካከል ማህተመ ጋንዲ ፤ ማንዴላ ፤ ማዘር ተሬሳና ማርቲን ሉተር ኪንግ ናቸው።

እነዚህ ሰዎች ምን ትልቅ አደረጋቸው? ማን ስም አወ ጣላቸው? ብለን ብንጠይቅ ትልቁ ሚስጢር ከራሳቸው አልፈው

ሌሎችን ለማገልገል ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኞች በመሆናቸው ነው። በተለይ ማዘር ተሬሳ ምንም አይነት የፖለቲካ ወንዘር የሌላቸው ከሌላው ተራ ህዝብ የተለየ ምንም ነገር ሳይኖራቸው የአለምን ህዝብና ነገስታት ልብ መሳብ የቻሉት ከራስ በወጣ ኑሮ ነው።

አንድ ቀን ባለሁበት አገር በቴሌቪዥን ዜና ስከታተል ስለ ማዘር ተሬሳ አንድ አስደናቂ ነገር ሰማሁ። ይህም በህንድ አገር ታዋቂ የሆነች ዘፋኝ ከማዘር ተሬሳ ጋር ተገናኝታ ስትመለስ ጋዜጠኞች እንዲህ የሚል ጥያቄ ይጠይቋት ነበር። ከማዘር ተሬሳ ጋር ባሳለፍሺው ጊዜ ምን ያየሽው የተለየ ነገር አለ? ይህች ታዋቂ ዘፋኝ ከማዘር ተሬሳ ያስገረመኝ ነገር ቢኖር ከእኔ ይልቅ እሳቸው ታዋቂ ሆነው ሳሉ ከሳቸው ጋር ባጠፋሁት ጊዜ ሁሉ ትልቅነት እንዲሰማኝ ያደረጉት እኔን መሆኑን አይቼ መመለሴ ነው አለች።

ምንም እንኳን ጌታ እየሱስን ከእነዚህ ታዋቂ ሰዎች ጋር ልናወዳድረው ባንችልም ጌታ የተጠቀመበት መመሪያ ግን አንድ ነበር። አምላክ ሰው ሆኖ ከሰው ጋር ህብረት ሲጀምር ጅማሬውን እንዲህ ብሎ ሃዋርያው ጳውሎስ በፊልጵስዩስ 2፥5-8 ላይ ገልጾታል። *«በጌታ እየሱስ የነበረው ሃሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን። እሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚ አብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባው ነገር አልቆ ጠረውም። ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ ለሞት ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳን የታዘዘ ሆነ።»*

ይህንን መመሪያ ለራሱ ብቻ ሳይሆን ደቀመዛሙርቱንም ለመጀመሪያ ጊዜ ሲመርጣቸው እሱ ከእነርሱ ጋር ራሱን ከዶ እንደመጣ እነርሱንም ማንም ሊከተለኝ የሚወድ ቢኖር ራሱን





ይካድ በማለት የህብረት ሁሉ መሰረትና ቁንጮ ራስን መካድ እንደሆነ አስተምሮአል።

እንግዲህ የትዳርም ጅማሬ እንዲህ ሊሆን ይገባል። ክብር ያለን ፣ ስም ያለንና የተማርን አዋቂ ሰዎች ልንሆን እንችላለን። ወደ ትዳር አለም ስንገባ ግን የባሪያን መልክ ይዘን ራሳችንን ባዶ አድርገን ተዋርደን ምንም ጥቅምና ክብር ሳንፈልግ የትዳር ጓደኞችንን ልናገለግል ይገባል።

በትዳር ጓደኞችን ውስጥ ያለውን የታመቀ ሃይል በማው ጣት ለህይወት የተሰጠውን የቤት ሥራ ፈጽሞ ወይንም ፈጽማ በጌታ ፊት አንተ በጎ ታማኝ ባሪያ አሰኪባል ወይንም አስኪ ትባል ድርስ ማገልገልን ይጠይ ቃል። ይህንን ላደረገ ሰው ዋጋው ከእግዚአብሔር ዘንድ ከፍ ያለ ነው።

**«በመጀመሪያ ሰይጣን ሰውን ከአምላኩ ለመለየት የተጠቀመበት መንገድ አሁን ደግሞ ሰውን ከጌታ ለመለየት የሚጠቀምበት የመጨረሻው ዘመን መሳሪያው ያው እኔነት ነው።»**

የአለማችን ችግር እኔነት ነው። ይህ እኔነት ሃዋርያው ጳውሎስ በ2ኛ ጢሞቴዎስ 3፥1 ከመጨረሻው ዘመን ምልክቶች በመጀመሪያ የተጠቀሰው ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉ የሚል ነው። በመጀመሪያ ሰይ ጣን ሰውን ከአምላኩ ለመለየት የተጠቀመበት መንገድ አሁን ደግሞ ሰውን ከጌታ ለመለየት የሚጠቀምበት የመጨረሻው ዘመን መሳሪያው ያው እኔነት ነው።

## *ሃሳብ*

ይህ የመጀመሪያውና የሰይጣን ወደ ሰው ወይንም ወደ ሄዋን የገባበት መንገድ ነው? ሰይጣን ሄዋን ስልጣን እንደነበራት በትክክል ያውቃል። ሂድ ብላ ብታዘው የሚታዘዝ የሰው ተገዢ ነበር። ይሁን እንጂ ይህ ሰይጣን አንድ ቀን በሥልጣን ላይ የነበረ ስለነበረ ወደ ሄዋን በማስገደድና በሃይል ሊመጣ አል ቻለም።

ነገር ግን ሰው ሊስት የሚችልበትን መልካም የሚመስል ግን በውስጡ መርዝ የሞላበትን ማር ግማሽ እውነትን በግማሽ ውሸት ቀላቅሎ አሳያት። ይህ የሰይጣን አሰራር ነው። ሄዋን የሰይጣንን ሃሳብ ስትቀበል ሃሳቡ ወደ እኔነት ተለውጦ በግል ውሳኔዋ እንድትሸነፍ አደረጋት። ሰይጣን ሄዋን እንድታደርግለት የፈለገውን ነገር ሲያስደርጋት መነሻው ትንሽ የምትመስል በጥ ያቄ መልክ የቀረበች ሃሳብ ነበረች። ያች ሃሳብ ነች አድጋ ፍሬ አፍርታ ለሞት ያበቃቻት።

በእግዚአብሔር ቃል ላይ ሦስት አይነት ሃሳቦች እንዳሉ እናያለን። አንደኛው የሰይጣን ሃሳብ ሲሆን ሁለተኛው የእግዚ አብሔር ሃሳብ ነው። ሦስተኛው ግን የራስ የሰው ሃሳብ ነው። እነዚህን ሃሳቦች ምን እንደሆኑ ማወቃችን ለትዳራችንም ሆነ ለምንኖረው ኑሮ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስላለው በአትኩሮ እን መለከታቸዋለን። ሃሳብ የነገር ሁሉ መነሻ ነው ካልን የአንድ ችግርን መፍትሄ ለማግኘት ስርና መሰረቱን መምታት አስፈላጊ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም።

## *የሰይጣን ሃሳብ*

ሰይጣን የራሱ የሆነ ሃሳብ አለው። በዮሃንስ ወንጌል 13፥2-3 «*እራትም ሲበሉ ዲያብሎስ በስምኦን ልጅ በአስቆሮቱ ይሁዳ ልብ አሳልፎ እንዲሰጠው ሃሳብ አገባ።*» ከዚህ ጥቅስ እንደምናየው ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ እንዲሰጥ ሃሳቡን ያገኘው ከሰይጣን እንደሆነ ነው። ቃሉ ግልጽ ነው። ሰይጣን ነው ሃሳቡን ያገባው።





እዚህ ላይ ሰይጣን ይሁዳ ውስጥ ገባ ሳይሆን የሚለው ሃሳብ አገባ ነው። ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ከሰጠ በኋላ ንጹህ ሰው አሳልፌ ሰጥቻለሁ ብሎ የተቀበለውንም ገንዘብ ለካህናቱ በትኖ እራሱን ሰቅሎ ሞተ። ልብ በሉ መነሻው ሃሳብ ነው ፤ ፍጻሜው ግን ሞት ነው።

በዮሃንስ 10፥10 ላይ «*ሌባው ሊሰርቅ ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለሌላ አይመጣም።*» የሰይጣንን ሃሳብ ለመለየት ቀላል ነው። ምክንያቱም ጌታ በዚህ ክፍል እንደተናገረው ስርቆት ማረድና መግደል አለበት። ሰይጣን በትዳራችን ውስጥ የመ ለያየት ሃሳብ ሊያመጣ ይችላል። ምንም እንኳን በትዳር ውስጥ ያለው አለመስማማት ሁሉ ምንጩ ሰይጣን ብቻ ነው ባንልም አንድ ሃሳብ ቀርቦ ጭቅጭቅ ፤ ጠብ ፤ ሁከትና ሰላም ማጣትን ካመጣ ሃሳቡ ከሰይጣን ሊሆን እንደሚችል ማወቅ ያስፈልጋል።

ሰዎች በእግዚአሔር ስም እንኳን ትንቢትንና መገለጥን አምጥተው ከተለያዩና ከተጨቃጨቁበት መልእክቱ ከየት እን ደመጣ መመርመር ተገቢ ነው። የሰይጣን ሃሳብ ሁልጊዜ በሰ ዎች ላይ ጉዳትን ፤ ሃዘንን ፤ ለቅሶን ፤ ትካዜንና ብሎም ሞትን የሚያመጣ ነው።

በቤታችን ውስጥ ሰይጣን ሃሳቡን እንደ ላከ ከእግዚ አብሔር ቃል መመዘኛ አለ። ሰይጣን ሲናገር ያስጨንቃል ወይንም ሰላም ይነሳል አለዚያ ያቻኩላል። ፈጽሞ ጊዜ አይሰ ጥም ምክንያቱም በጊዜ ውስጥ አስበን አውጠንጥነን የእግዚ አብሔርንም ድምጽ በሚገባ ሰምተን እንዳንወስን ነው።

ሰይጣን ያስገድዳል ወይንም የሰውን ፈቃድ አያከብርም። በትዳራችን ውስጥ የምናደርገው ነገር ሁሉ የሌላውን ሰው ፈቃድ እየጣሰ ያለ ፈቃዱ የሚደረግ ከሆነ ከሰይጣን ነው። ሌላው ሃሳቡ ከሰይጣን እንደሆነ መለያችን ከእግዚአብሔር ቤትና ከቅዱሳን ያርቃል ይለያል።

እንደዚህ ያሉ ነገሮች በቤታችን ካየን የሚያስፈልገን ውይይትና ምክር ሳይሆን ተቃውሞና በእየሱስ ክቡር ስም ጠላታችንን ማሰር ነው። ይሀንንም ስናደርግ ያልተስማማንበትን ሃሳብ ሰሙን እየጠራን ያንን መንፈስ በእምነት መቃወም ያስፈልጋል።

## *የእግዚአብሔር ሃሳብ*

በኤርሚያስ 29፥29 ላይ ጌታ ለእስራኤል ህዝብ ሲናገር *«ለእናንተ የማስባትን ሃሳብ እኔ አውቃለሁ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም ሃሳብ ነው እንጂ የክፋ ነገር አይደለም።»* እንዲዚሁም በሃዋርያት ስራ 13፥36 ላይ *«ዳዊትም በራሱ ዘመን የእግዚአብሔርን ሃሳብ ካገለገለ በኋላ አንቀላፋ ከአባቶቹም ጋር ተጨምሮ መበስበስን አየ።»*

ከእነዚህ ሁለት ጥቅሶች እንደምናየው እግዚአብሔር ደግሞ የራሱ የሆነ ሃሳብ አለው። ይህ የእግዚአብሔር ሃሳብ እስራኤላውያን በሃጢአታቸው ምክንያት ወደ ባቢሎን ተማርከው ሄደው በነበረበት ጊዜ እንኳ ለህዝቡ ያለው ሃሳብ ፍጻሜና ተስፋ ያለው የሰላም ሃሳብ እንጂ ፈጽሞ የክፉ ነገር እንዳልሆነ እናያለን።

እግዚአብሔር ለህዝቡ ያለው ሃሳብ ይህ ነው። ከዚህ ውጪ ፈጽሞ ሊሆን አይችልም። ያለንበት ትዳር የማይመች ፣





ያልተሳካና ችግር ያለው ቢሆንም ቅሉ የእግዚአብሔር ሃሳብ ለዛ ቤተሰብ ፍጻሜ ያለው መልካም የሆነ የሰላም ሃሳብ ነው።

በቤታችን ላለው ማንኛውም ሃሳብ የእግዚአብሔር ለመሆኑ መመዘኛ ሃሳቦች ከእግዚአብሔር ቃል አለ። የእግዚአብሔር ሃሳብ ሲሆን ሰላም ይሰማናል። ደስ ደስ ይላል። በውጪ የሚታየው ነገር የሚያስፈራ ቢመስል እንኳን ውስጣችን በጸና ሰላም ይሞላል። የጌታ ሲሆን አያቻኩልም ፣ እንድናስበበትና እንድንጸልይበት ሰፊ ጊዜ ይሰጣል። ደግሞም አያስገድድም። የሰውን ፈቃድ ያከብራል ያ ሰው እስኪገባው እስኪረዳ ድረስ ይጠብቃል ይታገሳል።

## *የሰው ሃሳብ ነው*

ከላይ ያየናቸውን ሁለቱን ሃሳቦች ከሞላ ጎደል ብዙ ክርስትያን ያውቃቸዋል። ለብዙ ቤት መፍረስና መለያየት ምክን ያት ከሆነው መካከል አንዱ ግን የሰው ሃሳብ ነው።

በማቴዎስ 16፥13-23 ድረስ ያለውን ታሪክ በምናነብበት ጊዜ ጌታ እየሱስ የሰውን ልጅ ማን እንደሆን ይሉታል? ብሎ ስጠየቀው ጥያቄ ጴጥሮስ ከሰማይ በሆነ መገለጥ አንተ የህያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ በማለት መልስ ይሰጣል። ጥቂት ቆይቶም ጌታ ስለ ሞቱና መከራው ለደቀመዛሙርቱ መናገር በጀመረበት ጊዜ ያው ጴጥሮስ ጌታን ወደ ጎን ወስዶ ጌታ ሆይ አይሁንብህ ብሎ ሊገስጸው ጀመረ። ጌታም ዘወር ብሎ *«በኋላዬ ሂድ አንተ ሲይጣን የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና እንቅፋት ሆነህብኛል»* በማለት ሲገስጸው እናያለን።

እዚህ ላይ ልብ ማለት ያለብን የተገሰጸ የሚመስለው ጴጥሮስ ይሁን እንጂ ጌታ በቀጥታ የተናገረው ሰይጣንን ነው። ሰይጣንን ሲገስጸው ግን የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታ

ስብዕና በማለት ሰይጣን የመጣበትን መንገድ በማስተዋል ለይቶ ነው። ከላይ የሰይጣንን ሃሳብ ምን እንደሆነ ባየንበት ጊዜ ሃሳቡ የመግደል ፣ የማጥፋትና የማረድ እንደሆነ አይተን ነበር። ስለዚህ ሰይጣን በምንም ተአምር ጌታን አትሙት አይሁንብህ ሊለው አይችልም። ነገር ግን ቅንና መልካም በሆነው በሰው ሃሳብ ውስጥ ተሰውሮ አይሁንብህ በማለት ከእግዚአብሔር ታላቅ አላማ ሊያስቀረው ሲሞክር እናያለን።

ሃሳቡ መልካም የሆነና ቅንነት ያለበት ነው። ማንም ሰው ልሙት ቢል ማንኛውም ሰው እንዴት እንዲህ ትላለህ ብሎ ቢገስጽ አስፈላጊ ግስጻ ነው። ሆኖም ግን ያ ሃሳብ የማን ነው? የሚለው ጥያቄ መልስ አስካላገኘ ድረስ ግሳጼውን መመርመር አስፈላጊ ይሆናል።

እንግዲህ ስለዚህ ነው መልካም የሆነ ሃሳብ ሁሉ የእግዚአብሔር አይደለም የምንለው። ዛሬ ብዙ ቤተሰብ ይህንን ባለማስተዋል ለቤቱ አሰቤ ነው። ይጠቅማል ብዬ ነው። እኔ እኮ መች ክፉ ተናገርኩ እያሉ መልካም ሃሳብ የያዙ መሰሎ እቸው ሳያውቁ የሰይጣንን አላማ የሚያስተናግዱት።

የሰው ሃሳብ መልካምና ቅንነት የተሞላው ስለሆነ ለመለየት አስቸጋሪ ነው። ይሁን እንጂ ያ ሃሳብ አስቀድሞ እግዚአብሔር ከተናገረው ጋር የሚጋጭ ከሆነ የቱንም ያህል መልካም ይምሰል እንጂ መቃወም አለብን። በእግዚአብሔር ሃሳብ ላይ የሚነሳውን ከፍ ያለውን የሰውን ሃሳብ ሁሉ እናፈርሳለን። 1ኛ ቆሮ 10፥5 ማንኛውም ሃሳብ መልካም ሆኖ እያለ በመካከላችሁ ጭቅጭቅን አለመስማማትን ካመጣ ከበስተጀርባው የሚሰራ ክፉ መንፈስ ሊኖር እንደሚችል በመገን ዘብ በጋራ መቃወም ይገባል።



፫

# ጋብቻና አላማው

የጋብቻ አላማን በሁለት ክፍሎ ማየት ይቻላል። አን ደኛው ተጋቢዎቹ ራሳቸው እንደ እግዚአብሔር ፍጡር የተፈ ጠሩበትን አላማ ማወቅ ሲሆን ሁለተኛው ጋብቻ ያስፈለገበት አላማው ምን እንደሆነ ማወቅ ነው።

## *የተፈጠሩበትን አላማ ማወቅ*

መቼም እንኳን እግዚአብሔር ይቅርና ሰውም አንድን ነገር በሚሰራበት ጊዜ የራሱ የሆነ አላማ እንደሚኖረው ግልጽ ነው። በዚህ አለም ላይ የተፈጠሩት ፍጥረታት በሙሉ በአላማ ተፈጥረዋል። በእኛ አመለካከት አያስፈልጉም ያለ እነርሱ መኖር እንችላለን ብለን የምንገምታቸውን ነገሮች ሁሉ እግዚ አብሔር በጠለቀ አላማ ፈጥሮአቸዋል።

ሰው በምድር ላይ የሰራውን ነገር ስናይ አውሮፕላንን በአየር ላይ እንዲበር ፣ መኪናን በመንገድ ላይ እዲሽ ከረከር ፣ መርከብን ደግሞ በባህር ላይ እንዲሰፍ አድርጓል። ሦስቱም ነገሮች ለመጓጓዝ የሚያገለግሉ ቢሆኑም አሰራራቸው ግን ለየቅል ነው። የተሰሩበት መሳሪያና ቅርጹንም የሚወስነው እንዲሄዱ የተሰሩበት አላማ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ አንድን ነገር እንደሚገባ እንዳይሰራ የሚያደርገው ደግሞ ከተሰራበት አላማ ውጪ ልንጠቀምበት ስንሞክር ነው። አንድን መኪና ወስደን በውሃ ውስጥ እንዲሄድ ብናደርገው ለመሄድ ይቅርና ከናካቴው ለተፈጠረበት አላማ እንኳን እንዳይሰራ እናደርገዋለን።

አውሮፕላን በምድር ላይ መሄድ ይቻል እንጂ አሰራሩ በአየር ላይ እንዲበር ነው። በምድር ላይ የሚሆነው ለመነሳትና ለመውረድ ብቻ ነው። ልክ እንደዚሁ ሁሉ ትዳር በምድር ላይ ያለ እግዚአብሔር የሰራው ተቋም ይሁን እንጂ አላማውና ግቡ ፍጹም ሰማያዊ ነው።

**« ትዳር በምድር ላይ ያለ እግዚአብሔር የሰራው ተቋም ይሁን እንጂ አላማውና ግቡ ፍጹም ሰማያዊ ነው ።»**

ዛሬ ብዙ ተጋቢዎች ትዳርን የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ ይጠቀሙበታል። ከብቸኝነት ለመላቀቅ ፣ ከስጋዊ ምኞት ለመጠበቅና ልጆችን ለመውለድ ወዘተ. በመሳሰሉት ምክንያቶች ላይ የተመሰረቱ ጋብቻዎች ይደረጋሉ። እነዚህ ነገሮች ሁሉ አስፈላጊ መሆናቸው ግልጽ ነው። ነገር ግን የትዳር አላማ አይደሉም። ባለንበት አለም ላይ የተሳከለት ጋብቻ በፍቅር ላይ የተመሰረተ ነው ወይስ በአላማ ላይ የተመሰረተ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ጥናት ተደርጎ ነበር። ከጥናቱ የተገኘው ውጤት ሲታይ በአላማ ላይ ተመስርተው የተጋቡ ባለትዳሮች የሰላምና ረዘም ያለ የጋብቻ እድሜ እንዳላቸው ሲገለጽ በፍቅር ላይ ብቻ ተመስርተው የተጋቡ ሰዎች ግን ከተጋቡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ቤታቸው የጭቅጭቅና ሰላም የሌለበት ብሎም የአጭር ጊዜ ብቻ እንደሆን ተደርሶበታል።





ይህ የሚያሳየን የትዳሩ ጤንነት ያለው በምናገኘው የፍቅር ግብግብ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን በተጋባንበት አላማ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ነው። አንድ ጸሃፊ ስለ ትዳር እንዲህ ሲል ጽፎአል። ትዳር ሁለት የተለያዩ ደራሲዎች የሚጽፉት ሁለት የተለያየ የታሪክ ጽሁፍ ሳይሆን ሁለት የተለያዩ ደራሲዎች የሚጽፉት አንድ የታሪክ ጽሁፍ ነው።

ትዳር ሁለት ሰዎች አንድ ሆነው በአንድ አላማ አንድን የህይወት ታሪክ ጽፈው የሚያልፉበት እንጂ ሁለት ሰዎች በአንድ ቤት ጣራ ስር ተስማምተው ሁለት ታሪክ እየጻፉ የሚኖሩበት ህይወት አይደለም።

**«ትዳር ሁለት የተለያዩ ደራሲዎች የሚጽፉት ሁለት የተለያየ የታሪክ ጽሁፍ ሳይሆን ሁለት የተለያዩ ደራሲዎች የሚጽፉት አንድ የታሪክ ጽሁፍ ነው ።»**

አላማ የለሽ ወይንም አላማውን የሳተ ትዳር አሰልቺ ፣ አድካሚና ከቀን ወደ ቀን ብርሃኑ እየጨለመ የሚሄድ ባውዛ ነው። ብዙ ተጋቢዎች በእጮኝነት ጊዜ ያከማቹዋትን ትንሽ የፍቅር እሸት በልተው ከጨረሱ በኋላ ምን እንደሚያደርጉ ግራ ይገባቸዋል። የእጮኝነት ጊዜ የመነፋፈቁ ፣ መቼ ተያየተን ፣ መቼ ተገናኝተን ጊዜው ይቀርና በሰርግ ማግስት በየቀኑ በሳሎን ፣ በወጥ ቤትና በመኝታ ቤት ሁሉ ሌላ የሚታይ ሰው ይጠፋና እርስ በርስ መፋጠጥ ይመጣል። ወሬውም የቤቱም ሥራ ያልቃል ከዛም ስራ የፈታ አእምሮ የሃጢአት ቢሮ ነው ፤ እንዲሉ የትዳር ጓደኛቸውን ስህተት መፈለግ ይጀመራል። ቀድሞ የሚያስደስተው ነገር ሁሉ የሚያስደስተው ለካ በወረት ስለሚደረግ ነበር። አሁን ግን በእጅ የያዙት ወርቅ ከመዳብ ይቆጠራልና ሁሉ ነገር ጣእም ያጣ ይመስላል።

ዋናው መሰረታዊ ችግር በተጋቢዎቹ አእምሮ ውስጥ ለምን እንደተጋቡና ለህይወት ያላቸው እይታ አለመስተካከሉ ነው። ከጥቂት አመታት በፊት እኔና ባለቤቴ የመኖሪያ ቤት ለመስራት እድል አግኝተን ነበር። ቤት የመስራት ሃሳብ ከመጣ ጀምሮ ቤታችን ተለወጠ ወሬአችን ስለ ቤቱ ሆነ። አሁን መሰረት ተጣለ አሁን ጣራ ተመታ አሁን ቀለም ተቀባ የቱን እቃ ለየትኛው ክፍል ስንል ሳናውቀው ስንቀራረብ ሲያወያየን ሥራው ችግራችንን እንዳናይ ሲያደርገን አየሁ።

ለካ ችግሩ ሥራ የፈታው አእምሮአችን እንጂ እኛ አልነበርንም። የእኛ በአራትና አምስት ወር ውስጥ ተሰርቶ የሚያልቀው የቤት ሥራ ይህን ያህል ካቀራረበንና ቤታችንን ሳናውቀው ከለወጠ እግዚአብሔር የሰጠን የህይወት ዘመን የቤት ሥራችን ደግሞ በምድር ያለውን ዘመናችንን ሁሉ ምን ያህል ፍሬያማና የበረከት እንዲሆን ባደረገ።

ወንድሞቼና እህቶቼ ይህንን ጽሁፍ እያነበባችሁ ያላችሁ ሁሉ ለጥቂት ጊዜ አረፍ በሉና ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ሞክሩ። ለመሆኑ እኔ ማን ነኝ? በዚህ ምድር ላይ ልሰራው የተሰጠኝ ሥራ ምንድን ነው? ከትዳር ጓደኛዬ ጋር በማቀናጀት ምን ቁም ነገር በምድር ላይ ሰርተን ልናልፍ እን ችላለን? እነዚህ ጥያቄዎች ሁሉ ለብዙ ሰው በአምስት ደቂቃ ውስጥ መልስ የሚገኝላቸው አይደሉም።

በእርግጥ አንዳንድ ሰው ገና ነፍስ እንዳወቀ ማን እን ደሆነና ምን ሰርቶ ማለፍ እንዳለበት ለማወቅ የታደለ አለ። አንዳንዶች ግን ይህን አይነት እድል አልተሰጠን ይሆናል። ይሁን እንጂ ሰው የህይወት ዘመን ሥራውን ሳያውቅ እንዲኖር የተፈጠረ የለም። ታድያ ይህንን የህይወት ዘመን ጥያቄ እን ዴት አውቃለሁ? ለምትሉ ሁሉ ለጥያቄው መልስ መስጠት የሚያስችሉ ሃሳቦችን በጥቂቱ ከዚህ በታች ልጠቁም።





እኔ ማን ነኝ? ብለን ስንጠይቅ እኔ ዶክተር ነኝ ፣ አርቲስት ነኝ ፣ አስፖርተኛ ነኝ ፣ ሰባኪ ነኝ ፣ ዘማሪ ነኝ ፣ ወይስ ነጋዴ ነኝ ወዘተ... ማለታችን ነው። እነዚህም ነገሮች እንኳን ራሳቸው ዘርፈ ብዙ ስለሆኑ የትኛውን እንደሆንን ለማወቅ ያስቸግራል።

የእውር ሰው አለም በሚነካው ነገር የተወሰነ ነው። የአላዋቂ ሰው አለም በሚያውቀው እውቀት የተወ ሰነ ነው። የታላቅ ሰውም አለም በሚያየው ራእይ የተወሰነ ነው። እን ዲሉ በአለም ላይ ያሉት ታላላቅ ሰዎች ሁሉ የታላቅነታቸው ጅማሬ እይታቸው እንደሆነ ይነገራል። ወን ድሜ መኖርን ስታስብ ምን ይታይ ሃል? ይህ እይታ በሥጋ አይን የሚ ታየው ሳይሆን በውስጠኛው አይን ዘሊናህ ምን ይታይሃል?

> «የእውር ሰው አለም በሚነካው ነገር የተወሰነ ነው። የአላዋቂ ሰው አለም በሚያውቀው እውቀት የተወሰነ ነው። የታላቅ ሰውም አለም በሚያየው ራእይ የተወሰነ ነው።»

የኔ እህት መኖርን ስታስቢ ምን ይታይሻል? በሌላ አማርኛ ሌሎች ሰዎችም ሆኑ አንቺ ሲታደርጉት ወይም ሲያደርጉትና ሲናገሩት ደስ የሚልሽ ነገር ምንድን ነው? ማንነታችን ስናደርገውም ሆነ ስናስበው ወይም ሌሎች እንኳን ሲያደርጉት ደስ የምንሰኝበትና ውስጣዊ እርካታ የሚሰጠን ነገር ነው።

እውነተኛ ደራሲ ህይወቱ ሁሉ የተያያዘው ከጽሁፍ ጋር ነው። ከኪሱ ብእር አይጠፋም አእምሮው ሁልጊዜ ስለ ሚጽፈው ነገር በማሰብ የተያዘ ነው። እያወራ ፣ እየበላ ፣ እየተጫወተ ልቡ የታሰረው ግን በጽሁፉ ላይ ነው። እንደ ሙዚቀኛ የሆነ ሰው የሙዚቃ መሳሪያ ላይ በቀን አስራ ስድስት ሰአት እየተቀመጠ ሳይሰለቸው ዘመኑን ሁሉ መኖር ይችላል።

ማንነታችን በለያችን ላይ የተለጠፈ ውጫዊ አካል ሳይሆን በእኛ ውስጥ ያለ የህይወታችን ሞተር ነው፡፡

**«ህይወትን ስኬታማ የሚያደርገው ልትይዘው የምትፈልገውን ነገር ለመያዝ በመሮጥ ሳይሆን የያዝሀን ነገር እንዲሰራ በመያዝ ነው።»**

ወንድሜ ሆይ ምንድን ነው ስትሰራ ፣ ስታወራ ብትውል የማትሰለቸው ነገር? ያ ማንነትህ ነው። ህይወትን ስኬታማ የሚያደርገው ልትይዘው የምትፈልገውን ነገር ለመያዝ በመሮጥ ሳይሆን የያዝሀን ነገር እንዲሰራ በመያዝ ነው።

እውነተኛ ማንነት በልብ ውስጥ ታላቅና የማያቋርጥ ፍላጎት ይፈጥራል። ማንነታችን እንደ ሳር ከላይ በቀላሉ የሚታጨድ ሳይሆን ነገር ግን ዘጥልቀት ውስጥ ያለ ተቆፍሮ የሚወጣ የህይወት ማእድን ነው።

ዘምሳሌ 20፥5 *«የሰው ልብ ሃሳብ እንደ ጥልቅ ውሃ ነው። አስተዋይ ሰው ግን ከዚያ ቀድቶ ያወጣዋል»* ይላል። ጥበበኛው ሰለሞን ሰው በራሱ ውስጥ እግዚአብሔር ሰውሮ ያስቀመጠው የከበረ ነገር ማውጣት የሚችለው ራሱ ሰውየው ነው ይለናል። እውነተኛ ማንነት ከጥልቅ የሚቀዳ ስለ ሆነ ጥልቀቱን መድረስ የሚችል የተድንዱ ባለቤት የሆነው ሰው ብቻ ነው።

እዚህ ላይ ታድያ በውስጤ ያለውን ይህ ጥልቅ የሆነ እግዚአብሔር በሰው ሁሉ ውስጥ ያስቀመጠው ጸጋ ስጦታ ችሎታ የማወጣው እንዴት ነው? የሚል ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ ነው። ዘዚህ አለም ላይ በህይወታችን የኛ የሆነውና አለን የምንለው ነገር ሁሉ ይብዛም ይነሰም እንጂ ጊዜአችንን የሰጠነው ነገር ነው። ጊዜ ያልሰጠነው የእኛ የሆነ ነገር የለም።





ተማሪው ለትምህርቱ ፣ ገበሬው ለእርሻው ጊዜ እንደሰጠ መጠን ውጤትን ያያል። ልክ እንደዚሁም ሁሉ አንድ ሰው ከራሱ ጋር የሚመካከርዘት በውስጤ ያለው ነገር እግዚ አብሔር የሰጠኝ ስጦታ ምንድን ነው? ብሎ ለማሰብና ለመጸለይ ጊዜ መስጠት ያስፈልጋል።

ጊዜ ያልሰጠነው የተባረከ ነገር ምን አለ? ተማሪው ባጠናበት ሰአት መጠን ውጤቱ ይወሰናል። ነጋዴው በነገደበት ሰአት መጠን ያተርፋል። አንድ ሰው በህይወት ነገር ማትረፍ የሚችለው በውስጡ እግዚአብሔር ያስቀመጠውን ነገር ለማወቅ ጊዜ ሲሰጥና ከራሱ ጋር በጥያቄ መመካከር ሲችል ብቻ ነው።

እግዚአብሔር አምላክ ማንኛውንም ነገር ከመስራቱ በፊት ከራሱ ጋር ይማከራል። በዘፍጥረት 1፥26 *«ሰውን በመልካችን በምሳሌአችን እንፍጠር»* ብሎ ስለሴ ከራሱ ጋር ተማከረ። በኤፌሶን 1፥11 ላይ ደግሞ *«<u>እንደ ፈቃዱ ምክር</u> ሁሉን የሚሰራ እንደ እርሱ ሃሳብ አስቀድመን የተወሰንን በክርስቶስ ደግሞ ርስትን ተቀበልን።»*

**«እንደ እውነቱ ከሆነ ያለኝን ነገር ያመጣሁት እኔ እንጂ ያለኝ ነገር እኔን አላመጣኝም።»**

እንደ ፈቃዱ ምክር ሁሉን ይሰራል ሲል እግዚአብሔር ከራሱ ጋር ሳይማከር ፣ ፕላን ሳያደርግ ምንም ነገር አይፈቅድም ፤ አያደርግም ፤ ማለት ነው። እንደውም ዛሬ በእኛ ህይወት ያለው መዳንና በረከት ሁሉ ከዘመናት በፊት የታሰቡ የታቀዱና በሥላሴ የተመከሩ ከእግዚአብሔር ልብ በምክር የወጡ ናቸው።

ለዚህ ነው ጠቢቡ ሰለሞን በምሳሌ 4፥23 ላይ *«አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ የህይወት መውጫ ከእርሱ ነውና»* የሚለው። ህይወት በውጪው አለም ያለ ነገር

ሳይሆን በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ ያለ የታመቀ ሃይል ነው። ይህ የታመቀ ሃይል መውጫው የሰው ልብ ነው። እንግዲህ የህይወት መውጫ ልብ ከሆነ በልብ ውስጥ ምን እንደሚገባና እንደሚወጣ መጠበቅ አስፈላጊ ነገር መሆኑ ብቻ ሳይሆን በልብ ውስጥ ምን እንዳለ አውቆ ያንን በማውጣት ለመኖር መሞከር የሰውን ህይወት በእርካታ ይሞላል።

ህይወት ከውስጥ ወደ ውጪ ይፈሳል እንጂ ከውጪ ወደ ውስጥ አይፈስም። ያለኝ ነገር ማንነትን ሊሰጠኝ አይችልም። እኔ ግን ላለኝ ነገር ዋጋ እሰጠዋለሁ። ሰው ለራሱ ዋጋ የሚሰጠው ሲኖረው ወይም ህይወት ሊሳካለት ሊሆን አይገባም። እንደ እውነቱ ከሆነ ያለኝን ነገር ያመጣሁት እኔ እንጂ ያለኝ ነገር እኔን አላመጣኝም።

በአሜሪካ ውስጥ አንድ ታዋቂ የሆነ የአሜሪካን የእግር ኳስ ተጫዋች አንድ ቀን ጫማ ሊገዛ ወደ ጫማ መሸጫ መደብር ገባ። ይህ ሰው በስህተት የጫማው ቁጥር አነስተኛ የሆነን ጫማ እግሩ ውስጥ ለመለካት አስገባ። ልኩ እንዳልሆነ ባየ ጊዜ ሌላ ጫማ ገዝቶ ከሄደ በኋላ ይህ ሰው በስህተት ለክቶት የሄደው ጫማ በሃምሳ እጅ ዋጋው ጨመረ።

ዋጋው የጨመረበት ምክንያት ይህ ታዋቂ የሆነው ሰው እግሩን ጫማው ውስጥ ስላስገባ ነበር። ታድያ ጫማው ነው ለሰውየው ዋጋ የሰጠው ወይንስ ሰውየው? መልሱ ግልጽ ነው። ታዋቂው ሰው ነው የጫማውን ዋጋ ከፍ ያደረገው። ያለን ገን ዘብ እውቀት ትዳር ወዘተ... ለእኛ የተፈጠሩ እንጂ እኛ ለእነርሱ አልተፈጠርንም። እኛ ዋጋ እንዲኖራቸው እናደርጋልን እንጂ የነገሮች መኖርም ሆነ አለመኖር በሰው ላይ የሰውን ዋጋ ሊጨምርም ወይም ሊቀንስ አይገባም።

ብዙ ሰው ህይወትን የሚለካው በሌላ ሰው ስኬት ነው። ህይወት ግን የሚለካው በሰው ውስጠኛ ክፍል ነው። ሌላው





ተሳክቶለት አውጥቶ ያሳየው ከውስጥ መቅዳት ስለቻለ ነው። ያ ማለት ግን ሰው ሁሉ ያንን በማድረግ ይሳካለታል ማለት አይደለም። የኔ ስኬት ያለው በእኔ ውስጥ ነው። የኔ ነገ በእኔ ውስጥ ነው። እኔ ውስጥ ያለውን ካየሁት ፤ ያየሁትን ደግሞ መቅዳት ከቻልኩ ያኔ የህይወትን ትርጉም ከእኔ ዘለፈ መልኩ ለሰው ሁሉ ይታያል።

ትዳራችሁን ከበላይ ለማስቀመጥና ጌታ እንዳለው ለመ ስወር በማይቻልበት ተራራ ላይ ለማድረግ ማን መሆናችሁን ማወቅና አንዱ ሌላው በውስጡ ያለውን ስጦታ እንዲያውቅ በመርዳት በጋራ ለቤታችን ሳይሆን ለአለም የሚበቃ ሥራ መስራት እንችላለን። ከዚህም በላይ ደግሞ ሥራ ፊት ስለማያደርገን የትዳር ጓደኞችንን ስህተት በመፈለግ በትንሽ ትልቁ በጭቅጭቅ ክብረት ለመጫር እድል አይሰጠንም።

## *የትዳር አላማን ማወቅ*

እስካሁን ያየነው ተጋቢዎቹ ራሳቸው እንደ እግዚአብሔር ፍጡር የተፈጠሩበትን አላማ ማወቅ ምን ያህል ለትዳሩ ትልቅ አገዛ እንደሚሰጥ ቢሆን ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ትዳር ወይም ጋብቻ ያስፈለገበት አላማው ምን እንደሆነ እናያለን።

እግዚአብሔር አምላክ ሰውን በመልኩና በአምሳሉ ፈጥ ሮታል። ይህ የእግዚአብሔር መልክ ልዩ ልዩ ገጽታ ያለው ቢሆንም ከገጽታዎቹ መካከል አንዱ ግን እግዚአብሔር አንድም ሦስትም መሆኑ ነው።

ሥላሴ የሚለውን ቃል የሥነ መለኮት አስተማሪዎች የተለያየ ምሳሌ በመስጠት ለማስረዳት ይሞክሩ እንጂ ማንም ሰው ትክክለኛ ትንታኔ ሰጥቶ እንዲህ ነው ማለት አይችልም። ምክንያቱም ሥላሴ የእግዚአብሔር ማንነት ከታሰረበት ሚስ

ጤራት መካከል አንዱ በመሆኑ ነው። እግዚአብሔርን ለመ ረዳት በጣም አስቸጋሪ ከሚያደርጉት ነገሮች መካከል አንዱ አንድም ሦስትም መሆኑ ነው።

የእግዚአብሔር ማንነት አንዱ አንድም ሦስትም ወይንም አንድም ብዙም መሆኑ ነው። ሥላሴ ስንል እግዚአብሔር አምላክ ራሱን በሦስት መንገድ የገለጸ አንድ አምላክ ማለታችን ነው። ምንም እንኳን ሥላሴ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰ ባይሆንም የሥላሴ ማንነትና ተግባር ግን በግልጽ ተጠቅሶ እናያለን።

ሥላሴ የሚለው ቃል በግእዝ ሡሉስ ከሚለው የተገኘ ሲሆን ሡሉስ ማለት ደግሞ ሦስት ማለት ነው። ይህም አንድ እግዚአብሔር ራሱን በሦስት መንገድ የገለጸ ለማለት ነው። ሥላሴ አንድም ሦስትም ነው። ስሙም በሦስት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ተብሎ ይጠራ እንጂ መጽሃፍ ቅዱስ አንድ አምላክ እንደ ሆነም በግልጽ ይናገራል ። ዘዳግም 6፥4 ይህንን የሥላሴን ሃሳብ ለማንሳት የፈለኩት ስለ ሥላሴ ማብራሪያ ለመስጠት ፈልጌ ሳይሆን ትዳርን በተመለከተ እግዚአብሔር የገለጠልኝን ሚስጥር በጥቂቱ ለማካፈል ያህል ነው።

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው በራሱ አምሳልና መልክ ነው። ከእግዚአብሔር መልክ መካከል ደግሞ አንዱ መልኩ እሱ አምላክ የሆነው አንድም ብዙም መሆኑ ነው። ይህ የእግዚአብሔር መልክ ከሆነ እንግዲህ ሰውንም ሲፈጥር ይህንን መልክ በሰው ላይ ማሳየቱ ግድ ነው።

አስቀድሞ አዳም እንደተፈጠረ እግዚአብሔር አይቶ መልካም እንደሆነ ተናግሮ ነበር። ይሁን እንጂ በምዕራፍ ሁለት ላይ ደግሞ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም አለ። መልካም አይደለም ያለው በአዳም አፈጣጠር ላይ





ስህተት ተሰርቶ ስለነበር ሳይሆን አዳም እግዚአብሔርን ከሚመስልበት መልኩ አንዱ ገና ስላልተገለጸ ነበር።

እግዚአብሔር መልኩ አንድም ብዙም ከሆነ አዳም ደግሞ ይህንኑ መምሰል ነበረበት። ስለዚህም አንድ ብቻውን የነበረውን አዳም ሄዋንን በመፍጠር ሁለት አደረጋቸው። ይህም ደግሞ እግዚአብሔርን አላስ መስለውም። ምክንያቱም እግዚአብሔር አንድ ብቻ አይደለም እንዳልን እግዚአብሔር ሦስትም (ብዙ) ብቻ አይደለም። ነገር ግን በአንድ ጊዜ አንድም ሦስትም ነው።

**«ባልና ሚስት አንድ ስለሆኑ ይስማማሉ እንጂ አንድ ለመሆን አይስማሙም። አንድነታቸው መስማማት ፈጥሮላቸዋል እንጂ መስማማታቸው አንድነትን አይፈጥርላቸውም።»**

በስላሴ መካከል አን ዱን ከሌላው ልዩ የሚያ ደርገው ነገር ግልጽ ሆኖ አያለ አንድነቱ ደግሞ ፈጽሞ ሊከድ የማይቻል መሆኑ ይታያል። ልክ እንደዚሁ ባልና ሚስት የተለያዩ ፍጥረቶች መሆናቸው ሊካድ የማይቻል እውነት ነው። ይህ ልዩነታቸው ጉልህ ሆኖ እንደሚታይ ሁሉ አንድነታቸውም ከልዩነታቸው ጋር በእኩል ደረጃ ግልጽ ሆኖ እንዲታይ አድርጎታል።

እግዚአብሔር ጋብቻን የመሰረተው አዳምና ሔዋን አምላ ካቸውን እንዲመስሉ እነዚህ ሁለቱ መጋባት ነበረባቸው። ዘፍጥረት 2፥25 ስለዚህ *«ሰው እናቱና አባቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይጣበቃል»* በማለት ሁለት የነበሩ ሳሉ እግዚአብሔርን ይመስሉ ዘንድ አንድ አደረጋቸው። አሁን ሰው አምላኩን መሰለ።

ሥላሴ የአብ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ የስምምነት ኑሮ ሳይሆን አንድነትና ውህደት ነው። ባልና ሚስትም ተስማምተው እንዲኖሩ አልተፈጠሩም። አንድ ሆነው እንዲኖሩ እንጂ። ሁለትን ሰው ማስማማት በጣም ከባድ ነው። ምክንያቱም ሁለቱ አንድ እንዲሆኑ ሁለቱንም ማፍረስ ስለሚጠይቅ ነውና። አንድን ሰው ማስማማት ግን እጅግ ቀላል ነው። ስለዚህ ባልና ሚስት አንድ ስለሆኑ ይስማማሉ እንጂ አንድ ለመሆን አይስማሙም። አንድነታቸው መስማማት ፈጥሮላቸዋል እንጂ መስማማታቸው አንድነትን አይፈጥርላቸውም።

በጋብቻ ምክር አገልግሎት ላይ ትልቁ ችግር ሰዎቹን በማስማማት አንድ ለማድረግ መፈለጋችን ነው። ይህንን ስናደርግ ይበልጡን ከአላማቸው በመለየት ችግሩን እናባብሳ ለን። ከዚህ ይልቅ ግን አንድ ስለሆኑ ሊስማሙ እንዲገባቸው ማሳየት ብንችል ብዙ ጊዜና ድካም እንቀንሳለን።

ፈሪሳውያን ወደ ጌታ እየሱስ መጥተው ሙሴ ሰው ሚስቱን ሊፈታ ቢፈልግ የፍችዋን ወረቀት ሰጥቶ ይፍታት ብሎ ፈቅዶልናል ፤ አንተ ምን ትላለህ ባሉት ጊዜ ጌታ እየሱስ ሲመልስ ከመጀመሪያው እንዲህ አልነበረም ሲል ይህንን ፍጹም ውህደት ከጋብቻ አላማ ጋር አገናዝቦ እግዚአብሔር ያጣ መረውን ሰው አይለየው በማለት ነበር መልስ የሰጠው።

እዚህ ላይ ልብ ማለት ያለብን ነገር ጌታ ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣው በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረውን ውህ ደት እንደገና ለማደስ መሆኑን ነው። ታድያ ሃጢአት ከእግዚ አብሔር የለየውን ሰው ዋጋ ከፍሎ ወደ አምላኩ ውህደት

**«ይህ በልዩነት አንድነት ሳይሆን ልዩ ልዩ የሆነው ለአንዱ ሲባል አንድ ሲሆን ነው።»**





በማምጣት አላማ ራሱን ሰጥቶ የመጣውን ጌታ ስለ ትዳር መለያየት መጠየቁ ፈሪሳውያን ምን ያህል የእግዚአብሔርን ትልቁን አላማ እንደሳቱ የሚያሳይ አይሆንምን? መጽሃፍትንና የእግዚአብሔርን ሃይል አታውቁምና ትስታላችሁ ተብሎ እን ደተጻፈ ፈሪሳውያን በትዳር ጉዳይ ስተው ነበር።

ይህ የሰማይ ውበት ነው። አንዱ ብዙ ሲሆን ብዙው ደግሞ ተመልሶ አንድ ሲሆን። ይህ በልዩነት አንድነት ሳይሆን ልዩ ልዩ የሆነው ለአንዱ ሲባል አንድ ሲሆን ነው። ልዩነታችን አንድነታችን እንዳይነካብን መጠበቂያ ወይንም አንድነታችን ልዩነታችንን አስካስጠበቀ ድረስ ብቻ የሚል አርማ ያለው ሳይሆን አንዱ በብዙ መልኩ ተፀንቶ ተመልሶ በውህደት በፍጹም አንድነት ሲኖር ማለት ነው።

የሥላሴ አንድነት በልዩነቱ እንዳይጋጭ የተያያዘ ሳይሆን አንዱ እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ ራሱን በብዙ መንገድ መግለጽ መፈለጉና መቻሉ ነው። ይህ ታላቅ ሚስጢር ነው። ልክ እንደዚሁ ባልና ሚስት ሁለት ሆነው አንድ ከሆኑ ቤተሰብ ብዙ ሆኖ አንድ ይሆናል። ከባም ሁብረተሰብ አገር እያለ ወደ አለም ሁሉ ይደርሳል።

**«አንድ የሚባል ነገር ሁሉ የብዙ ነገር ውህደት ውጤት ነው።»**

ከቤተሰብ ያልጀመረ አንድነት ወደ ቤተክርስትያን አይደርስም። ከቤተ ክርስትያን ያልተወለደ አንድነት አገርን አለምንም ፈጽሞ ሊደርስ አይችልም። ወንጌል በምድር ላይ እንዲሮጥ መን ደርደሪያው ቦታ ቤተሰብ ነው። ለዚህ ነው ጋብቻ በምድር ላይ ይሁን እንጂ ሰማያዊ ነው ያልኩት። የእግዚ አብሔር የመጀመሪያ አላማ ሲገባን በምድር ላይ ጋብቻ ምን ለመስራት እንዳለ እንገነዘባለን።

ይህ ታላቅ ሚስጢር በቤተ ክርስትያንም አላማ ላይ የተገለጠ ነው። ሃዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፥14-26 ላይ የቤተክርስትያንን አንድነት ከአካል አንድነት ጋር እያይዞ በአራት በመክፈል እንዲህ ሲል ጽፏል።

**1ኛ/ አካል ብዙ ብልቶች እንጂ አንድ ብልት አይደለም።**

አንድ የሚባል ነገር ሁሉ የብዙ ነገር ውህደት ውጤት ነው። ትዳርን ትዳር ያሰኘው ባል ብቻ አይደለም ሚስትም ብቻ አይደለችም። የሁለቱ ውህደት ነው እንጂ። ልክ እን ደዚሁም የቤተክርስትያንን አንድነት ስናይ የአንድ ሰው ወይንም የአንድ ስጦታ ውጤት አይደለችም። ቤተክርስትያን የብዙ ብልቶች ስጦታ በአንድነት ናት እንጂ።

**2ኛ/ ብልት ሁሉ አንድ አይነት አይደለም።**

በዚህኛው ሃሳቡ ላይ ሃዋርያው ብዙ የተለያዩ ብልቶች በአንድነት አንድን ቤተክርስትያን አንድን ቤተሰብ ሰጠ ይበል እንጂ እያንዳንዱ ብልት አንድ አይነት ነው አላለም። የተ ለያየው ብልት በአንድነት አንድን አካል ሰጡ እንጂ። ልክ እን ደዚሁም ሁሉ ባልና ሚስት አንድ ናቸው እንጂ አንድ አይነት አይደሉም። ፈጽሞ የማይገናኝና የተለያየ ስብእና አላቸው።

**3ኛ/ እግዚአብሔር እንደወደደ ብልቶችን እያንዳዳቸውን በአካል አድርጎአል።**

> **«ባልና ሚስት አንድ ናቸው እንጂ አንድ አይነት አይደሉም።»**

እያንዳንዱ ብልት ያለውን ቦታ ፣ ቀለምና ቅርጽ የያዘው እግዚአብሔር ለአካሉ እንደሚሆን አድርጎ አስቀ ምጦታል እንጂ በራሱ ፈቃድ አይ ደለም። ይህም እያንዳንዱ ብልት በአካል ውስጥ ስለ አካሉ ይኖራል





እንጂ ፈጽሞ ለራሱ እንደማይኖር ያሳያል። መኖራችን ወይንም ህልውናችን ለሌላው እንደሆነና ያለ ሌላውም ህልውና እን ደሌለን የሚናገር ታላቅ ሚስጢር ነው። ትዳርም የራስን ሙብት ማስጠበቂያና ለራስ ጥቅም የመኖሪያ ቦታ ሳይሆን በአንድነት ስለ ፈጠረው ጌታ አላማ አንድነቱን ጠብቆ የሚኖርበት ህይወት ነው።

**4ኛ/ ሁሉም አንድ ብልት ቢሆን አካል ወዴት በተገኘ።**

በዚህ በአራተኛው ክፍል ላይ የብልቶች ልዩ ልዩ መሆን አካልን ለማስገኘት ችሎአል። ስለዚህ እያንዳንዱ ብልት በራሱ ጠቃሚ ነው እንጂ አንዱ ብልት ሁሉንም ለመሆን መሞከሩ ወይንም ሁሉም ብልት አንዱን ብልት ለመሆን መሞከራቸው የአካሉን ህልውና እንደሚያጠፋ በግልጽ ያስቀምጣል።

ሁሉም አንድ ብልት ቢሆኑ አካል የለም ሲል ራሱ አካሉ በአካልነቱ እንዳይኖራ አካል ያደረጉት ብዙ ብልቶች ናቸው ማለቱ ነው። በትዳርም ውስጥ ትዳሩ የሁለቱ የተለያዩ ሰዎች ውህደት እንጂ በትዳሩ ላይ የአንዱ ሰው መጉላት ወይንም ማነስ ትዳሩን ትዳር ከመሆን ይለውጠዋል ማለት ነው። በትዳር አለም ውስጥ ያለን ሁሉ ይህንን እውነት መቀበል ብንችል ትዳራችን ምንኛ ለአለም ብርሃን በሆን።

አላማዬ ይህንን ክፍል ለማስተማር ስላይደለ በክፍሉ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ትምህርቶችን ለመዳሰስ አልፈለኩም። ነገር ግን አጉልቼ ለመናገር የፈለኩትን ሃሳብ ሃዋርያው በግልጽ በጥሩ ምሳሌ ስላስቀመጠው ያንን በጥቂቱ ለማብራራት ያህል ነው። ይህም ሃሳብ ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት በልዩነት አንድነት ሳይሆን አንድ ሆነን ግን ልዩ ልዩ ነን። ልዩ ልዩ (Unique) ነን እንጂ የተለያየን (Different) አይደለንም ለማለት ነው።

የእግዚአብሔር አላማው መለየቱ ሳይሆን ልዩ ያደረገኝ ነገር የሌላውን ጉድለት በመሙላት አካሉ ሙሉ ሆኖ እንዲታይ ማድረግ ብቻ ነው። በትዳር ውስጥ ሚስት የሚስትነት ሙብትና ክብሩዋን ለማስጠበቅ ባልም የወንድነት ክብሩንና ስልጣኑን ለማስጠበቅ የገቡበት አንድነት ሳይሆን ሊሰሩ ያሉት አንዱ ቤት ይሰራ ዘንድ ባላቸው ልዩነት ሳይሆን ግን ልዩ (Unique) የመሆን ባህሪያቸው የጎደለውን መሙላት ሊሆን ይገባል።

ትዳር በሁለት ሰዎች መዋደድ ወይም መስማማት ላይ የተመሰረተ ብቻ እንዳልሆነ ነገር ግን ፍጹም በሆነ የእግዚ አብሔር ተአምራታዊ አሰራር የሁለት ሰዎች ሁለትነታቸው እን ዲተጠበቀ ሆኖ እንደ አንድ ሰው ደግሞ አንድ የሆኑበት ፍጹም መዋሃድ ነው። ሃዋርያው ጳውሎስ ትዳር ሚስጢር ነው ያለው ለዚህ ነው። ሁለቱን አንድ ያደረገ አንድንና አንድን ደምሮ ውጤቱን አንድ ነው ማለት የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው። ስለዚህ ትዳር አላማውንና ሃሳቡን ተረድተን እንጂ አሰራሩን ተረድተን የማንኖረው በእምነት ላይ የተመሰረተ የሁለት ሰዎች ተአምራዊ ውህደት ነው።

ከላይ ያየነው የትዳር ትርጉም በእግዚአብሔር አይን ሲታይ ይህንን ይመስላል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ከሰው የሚያከብረው ትልቅ ነገር ፈቃዱን ስለሆነ ይህንን የባልና የሚስት አንድነት የመሰረተው በሰው ፈቃድ ላይ ብቻ ነው። ማንንም ሰው በቃሉ ላይም ሆነ በትንቢት አስገድዶ እግዚአብሔር በትዳር አያዋህድም። ትዳር በሁለቱ ተጋቢዎች ፈቃድና

> **«ትዳር አላማውን ና ሃሳቡን ተረድተን እንጂ አሰራሩን ተረድተን የማን ኖረው በእምነት ላይ የተመሰረተ የሁለት ሰዎች ተአምራዊ ውህደት ነው።»**





መፈቃቀድ ላይ ብቻ ተመስርቶ ቃል ኪዳን ሲገባ ለመጋባት የወሰኑትን ሰዎች እግዚአብሔር ሁለቱን ወስዶ አንድ ያደርጋቸዋል።

ለዚህ ነው ጌታ እየሱስ እግዚአብሔር ያጣመረውን ሰው አይለየው ያለው። ልብ ካልን ጌታ ሰው አይለየው እንጂ ሰይጣን አይለየው አላለም። ምክንያቱም ትዳርን ትዳር የሚያሰኘው የሁለቱ ተጋቢዎች በፈቃዳቸው አንድ ለመሆን መስማማት ሲሆን የሚለያቸውም የሁለቱ ተጋቢዎች ፈቅደው ለመለያየት መወሰን ብቻ ነው።

ትዳርን ለማፍረስ የሌሎች ሰዎች ጣልቃ ገብነት ወይንም ሰይጣን በትዳሩ ላይ የሚያመጣቸው ተጽእኖዎች ሊኖር አይችልም ለማለት ሳይሆን ከተጽእኖው ባሻገር ትዳር የሚፈ ርሰው ተጋቢዎች ለማፍረስ ሲፈትዱ ብቻ መሆኑን ለማሳየት ነው።

ከላይ ለማየት እንደሞከርነው ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም። ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ ብቻ ሳይሆን ሁለት ሆኖ በአንድ ቤት ይኖር ዘንድም ፈቃዱ አይደለም። ታድያ ሰው አንድም ሁለትም ሆኖ እንዲኖር ካልሆነ የእግዚ አብሔር አላማ በትዳር ላይ ምንድን ነው? የእግዚአብሔር ትልቁ አላማ ሁለቱ አንድ ሆነው በውህደት ይኖሩ ዘንድ ነው። ይህ የሰማይ ውበት ነው።

እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን ሁለት የተለያዩ ሰዎች በትዳር ውስጥ አንድ እንዲሆኑ ካስፈለገ አንዱ በአንዱ ውስጥ ተደባልቆና ተዋህዶ መኖር ግድ ነው። የተለያዩ ፍራፍሬዎች እንደ ብርቱካን ፣ ሙዝ ፣ ፓፓያና አናናስን አንድ ላይ አድርገን በፍራፍሬ መፍጪያ ውስጥ ብናስቀምጣቸው አንድ ላይ ስለተቀመጡ ተዋህደዋል ማለት አይደለም።

ነገር ግን ይዋሃዱ ዘንድ ያ መፍጨያ በውስጡ ባለው ስለት ሁሉንም በሚቆርጥበት ጊዜ እያንዳንዱ ፍሬፍሬ ወደ ውሃነት ይለወጥና አንዱ በአንዱ ውስጥ ሆኖ ፍሩት ጋንች ይባላል። ይህም የሁሉም አይነት ጣእም መልክና ቀለም አደባልቆ የያዘ ነው። ሁሉም በውስጡ አሉ ሁሉም ግን ቀድሞ በነበራቸው ማንነት አይነት የሉም።

ትዳርም ልክ እንደዚሁ ነው። ሁለት ሰዎች ተፋቅረው በትዳር ውስጥ ስለገቡ ብቻ ተዋህደዋል ማለት አይደለም። ነገር ግን በትዳር ውስጥ አንዳቸው በሌላቸው ውስጥ ይዋሃዱ ዘንድ የፍሬፍሬው መፍጨያ በስለቱ ማንነታቸውን እያሳነሰ ወደ ውሃነት ለውጦ እንዲዋሃዳቸው ሁሉ ባልና ሚስትም የሚዋሃዱት እኔነታቸው ተፈጭቶ አንዱ በሌላው ውስጥ ሲዋሃድ ብቻ ነው።

እኔነት እያለ ውህደት የለም። ለመዋሃድ እኔነትን መጣል አይነተኛ ነው። ይህ ለትዳር ብቻ ሳይሆን ጌታ እየሱስም ከሰዎች ጋር ለመዋሃድ የተጠቀመበት ብቸኛ መንገድ ነው። አማኑኤል እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሆነው ራሱን ጥሎ ራሱን ባዶ አድርጎ ነው።

ደቀመዛሙርት ጌታን ባዩት ጊዜ ከእርሱ ጋር ለመሆን ፈልገው ነበር። ጌታም ከእኔ ጋር አንድ ለመሆን መንገዱ ብሎ እኔን መከተል የሚወድ ማንም ቢኖር ራሱን ይካድ በማለት የውህደት መሰረቱ የራስን ማንነት መጣል እንደሆነ አስረግጦአል።



፬

# ጋብቻ ያከ ፍቺ

## ትዳር ሚስጢር ነው

ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን 5፥32 ስለ ጋብቻና ስለ ቤተክርስትያን ሲናገር *«ይህ ሚስጢር ታላቅ ነው። እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተክርስትያን እላለሁ»* በማለት ከዚህ ጥቅስ በላይ በባልና ሚስት መካከል ስላለው ግንኙነት የተናገረውን ሀሳብ በቤተክርስትያንና በክርስቶስ መካከል እን ዳለው አይነት ህብረት መሆኑን፥ እንደገናም ይህ ግንኙነት ደግሞ የእግዚአብሔር ሥራ ስለሆነ ሚስጢር ነው በማለት ከክርስቶስና ከቤተክርስትያን ጋር አያይዞ አስቀምጦታል። ይህን ሚስጢር ሚስጢር ያደረገው መንፈሳዊ ይዘቱ የጠለቀና በሰው አእምሮ ለመረዳት የሚያዳግት መሆኑ ነው።

አንድ ሰው በክርስቶስና በቤተክርስትያን መካከል ያለውን ግንኙነት ለመረዳት መገለጥ እንደሚያስፈልገውና መገለጡም በየጊዜው እያደገ ወደ ሙላት እስኪመጣ ድረስ እንደሚያድግ ሁሉ፥ የጋብቻንም ሚስጢር ለመረዳት መገለጥ ያስፈልገዋል።

መገለጡም የአንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በህይወት ጎዳና ውስጥ በየጊዜው የሚገለጥ የህይወት መጽሐፍ ነው።

የቤተክርስትያንና የክርስቶስን ኅብረት ሚስጢር በአንድ ቀን ተረድተን ሁሉን እንደማናውቀው ሁሉ ፣ የጋብቻንም ሚስ ጢር በአንድ ቀን መገለጥ ወይንም የተወሰነ ኮርስ በመውሰድ ወይንም የተለያዩ መጻሐፍቶችን በማንበብ የምንረዳው አይደለም። የጋብቻ ሚስጢር ሁለቱ ተጋቢዎች በየቀኑ እርስ በርስ የሚተዋወቁበትና የሚዋሃዱበት የህይወት ሂደት ነው።

## እግዚአብሔር መፋታትን ይጠላል

ሰው መንፈስ ፣ ነፍስና ስጋ እንዳለው ሁሉ እውነተኛ ጋብቻ የተጋቢዎች የመንፈስ ፣ የነፍስና የሥጋ ውህደትና መጣመር ነው። በዘዳግም 6፥4-5 እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖራቸው ስለሚገባ ህብረት ሲናገር ፥ *«እስራኤል ሆይ ፥ ስማ ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው ፤ አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን ፥ በፍጹም ልብህ ፥ በፍጹም ነፍስህ ፥ በፍጹም ሃይልህ ፥ ውደድ።»* በማለት አንድነቱ ሁለን ተናን የሚጠይቅ እንጂ ከሰው ማንነት ያስቀረው አንድም ነገር እንደሌለ እናያለን።

ልክ እንደዚሁ ጋብቻም የመንፈስ የነፍስና የስጋ መጣ መርን ይጠይቃል። የአንድ ጋብቻ ትክክለኛነት ተጋቢዎቹ ባላቸው የሥጋ ፣ የነፍስና የመንፈስ ውህደት ላይ የተመሰረተ ነው። የተጋቢዎች ህብረትና አንድነት በሥጋ ፣ በነፍስና በመን ፈስ ውህደት ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ሁሉ የጋብቻ ፍቺም በሦስት አይነት መንገድ ይገለጻል። ይህም ተጋቢዎች አስቀ ድመው በመንፈስ ከዛም በነፍስ በመጨረሻም በስጋ መፋ ታታቸው ነው።





ፍቺ የሚለው ቃል አንድ የሆነን ነገር ለሁለት መክፈል ስለሆነ ባልና ሚስት በሚፋቱበት ጊዜ አንዱን ነገር ለሁለት ስለሚከፍሉት ከፍተኛ ህመምና ስቃይ አለው። ይህ አንድነት በሰው እውቀትና አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን እግዚ አብሔር እራሱ ሁለቱን አንድ ያደረገበት ተአምር ነው። ለተመልካች ባይገባም እውነቱ ግን ባልና ሚስት በእርግጥ ሁለት ሳይሆኑ አንድ ናቸው።

*«ስለዚህ ሰው አባትና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ስጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነ በባችሁምን»* *(ማቴዎስ 19፥5-6)*

**«ፍቺ የሚለው ቃል አንድ የሆነን ነገር ለሁለት መክፈል ስለሆነ ባልና ሚስት በሚፋቱበት ጊዜ አንዱን ነገር ለሁለት ስለሚከፍሉት ከፍተኛ ህመምና ስቃይ አለው።»**

ባልና ሚስት በሚፋቱበት ጊዜ የብዙ ሰው ትኩረት የሥጋ ፍቺው ላይ ነው። ሰዎች በውጪ የሚታየውን የሥጋ ፍቺን በማየት ተፋቱ ይላሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ተጋቢዎቹ በሥጋ ከመፋታታቸው በፊት በመንፈስና በነፍስ ይፋታሉ። የስጋ ፍቺው ግን የነፍስና የመንፈስ ፍቺው ውጤት ነው።

ይህ የመንፈስና የነፍስ ፍቺ ምንድን ነው? እውነተኛ ክርስ ትያናዊ ጋብቻ መሰረቱ የእግዚአብሔር ቃልና የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። በእግዚአብሔር ቃል እውነት ላይ የተመሰረተ ጋብቻ በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ የተመሰረተ እንደ እግዚ አብሔር ቃል የሆነ ጋብቻ ነው። ይህም የህይወታቸው ትልቁ አላማ ተጋብቶ ምድራዊ ሃብትን አፍርቶ ልጆች ወልዶ ህይወትን

መኖር አይደለም። ትዳር አንዱ ከሌላው ጋር በመዋሃድ የተፈጠሩበትን የመኖር አላማ በማቀናጀት በጋራ ያንን አላማ ወደ ግብ ማድረስ ነው። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ያልተቆጠበ የመንፈሳዊ ህይወት አድገትና ከእግዚአብሔር ጋር ቀን በቀን የመኖርን ህይወት ይጠይቃል።

**«ትዳር አንዱ ከሌላው ጋር በመዋሃድ የተፈጠሩበትን የመኖር አላማ በማቀናጀት በጋራ ያንን አላማ ወደ ግብ ማድረስ ነው።»**

ተጋቢዎች ከዚህ ሃሳብ ርቀው የመንፈሳዊ ህይወታቸውን ችላ ሲሉ ፣ በጋራ መጸለይንና በጋራ የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት ሲያቆሙ ፣ የግል ፈቃዳቸውንም ለማስፈጸም ሲባክኑ ሳያውቁት ወደ መንፈሳዊ ፍቺ ውስጥ ይደርሳሉ። በመንፈስ አብሮ ከመፍሰስና የእግዚአብሔርን ምሪት ድምጹንና ሃሳቡን በመጠየቅ ወደሚገኝ መንፈሳዊ ሙላት ከመግባት ይልቅ ወደ መንፈሳዊ ድርቀት ይገባሉ።

ይህ መንፈሳዊ ድርቀትና ረሃብ ሳያውቁት ወደ ነፍስ ፍቺ ያመጣቸዋል። ይህም በሃሳብ ያለመጣጣምና አንዱ የሌላውን ፍላጎት ወደ መናቅ ፣ አንተ ትብስ አንቺ ትብሺ ከመባባል ይልቅ ወደ ቁጣና ምሬት ያመጣቸዋል። በመጨረሻም አንዱ ሌላውን ከማገልገል ይልቅ ወደ መጉዳት ሲመጣ ይህ የተበላሸ ኑሮ አንዱ በአንዱ ላይ እየተደመረ ወደ ስጋ ፍቺ ያደርሳቸዋል።

በሚልክያስ 2፥16 እግዚአብሔር መፋታትን እጠላለሁ ብሎአል። ፍቺ የባልና የሚስት መለያየት ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ተአምራዊ የሆነውን የእጁን ስራ ማፍረስ





ነው። ትዳር ከባልና ሚስት ፍላጎት ያለፈ ነው። ትዳር የእግዚአብሔር መንግስት የሚሰፋበት የመንግስቱ ልጆች መፈልፈያ ኢንኩቤተር ነው። ትዳርን ማፍረስ የእግዚአብሔርን መንግስት እንደማፍረስ ነውና።

ከፍሉን ጠጋ ብለን ካየነው እግዚአብሔር ባልና ሚስትን አንድ አካልና አንድ መንፈስ ያደረገበትን ዋና አላማ ይናገራል። ይህም የእግዚአብሔር ህዝቦች የሆኑ ልጆችን እንድትወልዱ ነው ይላል። ከዚህ ሃሳብ እንደምንረዳው ይህ የጋብቻ አላማ ከተጋቢዎቹ ያለፈና የእግዚአብሔር አላማ ማስፈጸሚያ እንደሆነ ነው።

*«እግዚአብሔር የህይወትን መንፈስ አንድ አድርጎ ጠብቆልን የለምን? እርሱም የሚፈልገው ምንድን ነው? ዘር አይደለምን? ስለዚህ መንፈሳችሁን ጠብቁ ማንም የልጅነት ሚስቱን አያታልል።» (ሚልክያስ 2፥15-16)*

**«ትዳር የእግዚአብሔር መንግስት የሚሰፋበት የመንግስቱ ልጆች መፈልፈያ ኢንኩቤተር ነው።»**

ዛሬ በዓለማችን የጋብቻ ፍቺ እንደ ትልቅ ከእስራት ነጻ መውጫ መንገድ ተደርጎ ስለተቆጠረ ሰዎች ቃል ኪዳናቸውን ለመጠበቅ ዋጋ ከመክፈል ይልቅ ለመለያየት ምክንያት የሚሆናቸውን በህሊናቸው ውስጥ ልክ ያለመሆናቸውን ክስ የሚገታላቸው ጥቅስ ይፈልጋሉ። በሚልክያስ 2፥15 ላይ ግን *«እግዚአብሔር ከእናንተ እያንዳንዱ ለሚስቱ የገባውን ቃል ኪዳን ላለማፍረስ ልዩ ጥንቃቄ ያድርግ»* በማለት መፋታትን ምን ያህል እንደሚጠላ ብቻ ሳይሆን ቃል ኪዳንን ምን ያህል እንደሚያከብር ይናገራል።

ጋብቻ እግዚአብሔር የሰራው ተአምራዊ ቤት ብቻ ሳይሆን በተጋቢዎቹ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ የቃል ኪዳን አን ድነት ነው። ተጋቢዎች በሰርጋቸው ቀን በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ቃል ኪዳን ሲገቡ ኪዳናቸው በሃዘንና በደስታ በበሽታና በጤንነት በማግኘትና በማጣት ሞት እስኪለየን ድረስ በማለት ቃል ኪዳን ይገባሉ።

**«ትዳር የታሰረው በተጋቢዎቹ ፈቃድና በቃል ኪዳናቸው ላይ ብቻ ነውና።»**

እነዚህ ነገሮች ሁሉ ሰው በሰውነቱ ሊደርሱበት የሚችሉ ችግሮች ናቸው። ይህ ቃል ኪዳን ግን ከችግሩ በላይ የሚያኖራቸው የትዳራቸው መጠበቂያና ማሰሪያ ነው። ትዳር የታሰረው በተጋቢዎቹ ፈቃድና በቃል ኪዳናቸው ላይ ብቻ ነውና።

ይህ በአንርሱ ቃል የጸናውን ኪዳን በሚልክያስ 2፥15-16 ላይ እንደሚናገር እግዚአብሔር በመንፈስና በስጋ አንድነት ያጸናዋል። የመንፈስ አንድነቱ እግዚአብሔር ራሱ ምስክር ሆኖ በማይታይ ማህተም የሚያትመው ስለሆነ ከተጋቡበት ቀን ጀምሮ እግዚአብሔር ራሱ የሚሰጠው ሞገስ ፣ ጸጋና አንድነት ከውጪ የሚያይ ሰው ሁሉ እስኪገነዘብ ድረስ ባልና ሚስት መሆናቸውን ሲያጸድቀው ፣ የስጋ አንድነቱን ግን በሚታይ የደም ቃል ኪዳን እንዲሆን አድርጎታል።

ይህ የደም ቃል ኪዳን አንድ ሴት ከባልዋ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ስታደርግ በባልዋ የሚወሰደው ክብረ ንጽሀና ነው። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ወንዱ ከሴቲቱ ክብረ ንጽህናዋን ሲወስድ የሚፈሰው ደም እግዚ አብሔር ራሱ በተፈጥሮ ያስቀመጠው የደም ቃልኪዳን ማሰሪያ ምልክት ነው።





ብዙ ሰዎች ሴት ልጅ ክብረ ንጽህናዋን የሰጠችውን ሰው አትረሳም ይላሉ። ይህም አንድ ሴት ክብረ ንጽህናዋን ሳትገደድ በፈቃድዋ ከሰጠችው ሰው ጋር መለኮታዊ በሆነ አሰራር ቃል ኪዳናቸው በስጋ የደም ቃልኪዳን መጽናቱን ያሳያል።

ማመንዘር የሚለው ቃል ከሀግ ሚስቱ ማለትም በስጋ አን ድነት (የደም ቃልኪዳን) ከገባላት ሴት ውጭ ወይም ወንድ ውጪ ሌላ ሰው ጋር የሚደረገው ግንኙነት ነው። ምንዝርና ያሰኘውም ትልቁ ሃጢአት የደሙ ቃል ኪዳን በመፍረሱ ምክን ያት ነው።

ስለዚህ ነው አንድ ሴት እስከ ጋብቻዋ ቀን ድረስ ክብረ ንጽህናዋን ጠብቃ መኖር ያለባት። ሴት ልጅ ካገባችው ሰው ጋር በቃል ብቻ ያልሆነ ነገር ግን እግዚአብሔር በስጋ በሆነ የደም ቃል ኪዳን ስላጸናው በፍቅር እስከ መጨረሻ ድረስ ለመኖር እንድትችል ያደርጋታል። ለወንዱም ቢሆን ይህ እውነት ነው።

እዚህ ላይ ምን አልባት ይህ እውቀት ሳይኖራት ወይንም በስህተት ወይንም በግዳጅ ክብረ ንጽህናዋን ያስወሰደች ሴት ጋብቻዋ አይባረክም ለማለት አይደለም። የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከሃጢአት ሁሉ ስለሚያነጻ አንድ ሰው ንስሃ እስከገባ ድረስ ንሰሃው እውነተኛ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር እንደገና እንደ ድንግል ሊያነጻው ይችላል። ይህም ማለት ከጋብቻው በፊት ንጽህናዋ የተወሰደ ሴት ስታገባ ልክ በድን ግልናዋ እንደተጋባች ሴት ከባልዋ ጋር ፍጹም የስጋ አንድነት ይኖራታል።

እግዚአብሔር የቃል ኪዳን አምላክ ነው። ከሰው ጋር የገባው የመጨረሻው ቃል ኪዳን በልጁ በእየሱስ በኩል የገባው የደም ቃል ኪዳን ነው። ይህም በመስቀል ላይ ስጋውን ቆርሶ

ደሙን አፍስሶ ከሰው ጋር የአንድነት ቃል ኪዳን ያደረገበት ነው። ስለዚህ ነው አንድ ሰው ክርስቶስን ትቶ ሌላን ነገር ቢያመልክ አመንዝራ የሚባለው። ይህ ግን መንፈሳዊ ምንዝርና ነው።

## በፈተና የሚጸና የተባረከ ነው

በእኔ እምነት ከሞት በስተቀር ሰው ሚስቱን ሊለይ አይገባውም እላለሁ። በጋብቻ ውስጥ አብሮ ለመኖር የሚያስቸግሩ ብዙ ነገሮች እንዳሉ አውን ቢሆንም ቃል ኪዳንን ጠብቀው እግዚአብሔርን ታምነው ከጠበቁት ለማንኛውም ችግር ከጌታ ዘንድ መፍትሄ አለ። ክርስትያን ችግርን በመሸሸ ያሸን ፋል ብዬ አላምንም። ችግሩን ግን ከእግዚአብሔር ጋር በማጋጠም በእምነት ማሸነፍ ይችላል ብዬ አምናለሁ።

ማንኛውም ትዳር ፍቅሩ ይፈተናል። ከጋብቻ በፊት ያለን ፍቅር እውነተኛ መሆኑንና አለመሆኑን የሀይወት ችግሮች በሙሉ ይፈትኑታል። ጥያቄው ፍቅራችን ይህንን ችግር ያልፋል ወይ? ነው። ወርቅ በእሳት እንደሚፈተን ሁሉ ትዳርም በችግር እሳት ይፈተናል። ብዙ ሰው መሸሽና ማፈግፈግ የሚጀምረው በዚህ ጊዜ ነው።

ያስቆብ 1፥2-7 - «... *ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እን ደሙሉ ደስታ ቁጠሩት ትእግስትም ምንም የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ሙሉአን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም።»*

ያስቆብ በፈተና ውስጥ ያሉትን አማኞች ማንኛውም ፈተናና ችግር ሰራው ትእግስትን ማስተማር ነው ይላቸዋል። ይህም ትእግስት እግዚአብሔር በእናንተ ውስጥ ሊሰራ ያለውን ነገር እንዲፈጽም ያደርጋል ይላል። ብዙ ሰው ግን በትዳሩ ውስጥ ችግር ሲገጥመው የሚሰማውን ሀመምና ስቃይ እንጂ





ከችግሩ ባሻገር እግዚአብሔር በሀይወቱ ሊሰራና ሊፈጽም ያሰበውን ታላቅ ነገር ማሰብ ይሳነዋል።

ከዚህም በላይ ያስቆብ ሰው በዚህ መከራ ውስጥ እንዴት መኖር እንዳለበት ባያውቅና ጥበብ ቢጎድለው ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን በእምነት ይለምን ፤ እግዚአብሔርም የሰው ፊት አይቶ ስለማያዳላ ጥበብን ይሰጠዋል በማለት በመከራ ያለ ሰው ከመከራ አምልጦ ይሸሽ ሳይሆን በመከራ ውስጥ በመጽናት እግዚአብሔር በሀይወቱ ሊሰራ ያለውን ነገር ሰርቶ እስኪጨርስ ድረስ ይጽና ይላል። በዚህ መከራ ውስጥ ግን ምን ማድረግ እንዳለበት ያውቅ ዘንድ ጥበብን ከእግዚአብሔር ይጠይቅ ብሎ በመከራ ውስጥ ሰው እንዴት መኖር እንዳለበት ይመክራል።

> **«ትዳር በእግዚአብሔር በመንግስት ውስጥ ለማገልገል የመስልጠኛ ቦታ ነው።»**

ብዙ ሰው የጋብቻንም ሆነ የሀይወትን ችግር ለማምለጥ የራሱ የሆነ ዘዴና መላምት አለው። እግዚአብሔር ግን በውሃም ውስጥ ሆነ በእሳት ውስጥ ማለፊያ መንገድ አለኝ ብሎአል። ሰው ይህንን ሲረዳ ብቻ ነው በዚያ ችግር ውስጥ ተሰርቶ ለእግዚአብሔር መንግስት የሚጠቅም የሚሆነው።

ትዳር በእግዚአብሔር በመንግስት ውስጥ ለማገልገል የመስልጠኛ ቦታ ነው። ስለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ የአንድ አገልጋይ መስፈርቶችን ሲዘረዝር ሰው ቤቱን ማስተዳደር ባይችል የእግዚአብሔርን ቤት እንዴት ሊያስተዳድር ይችላል ያለው።

ባለቤቴን ይቅር ካላልኩ እንዴት በቤተክርስትያን ውስጥ ያሉትን ይቅር እላለሁ? በባለቤቴ ፊት መዋረድ ካልቻልኩ እን ዴት በቤተክርስትያን ሰዎች ፊት ዝቅ እላለሁ? ለባለቤቴ ያለኝን ቃል ኪዳን ካላከበርኩ እንዴት ለእግዚአብሔርና ለቤተክርስትያን ያለኝን ቃል ኪዳን አከብራለሁ? በቤቴ ውስጥ ለተነሳው ችግር ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብን ጠይቄ መፍትሄ ካላመጣሁ በቤተ ክርስትያን ውስጥ ላለው ችግር እንዴት መፍትሄ አመጣለሁ?

ይህ የጋብቻ ፍቺ በቤተሰብ መካከል መብዛቱ ይመስለኛል በቤተክርስትያን ውስጥም ያለውን የእርስ በርስ ልዩነት ያበ ዛው። አገልጋይ ህዝቡን መታገስ ሲያቅተው ፣ ህዝብ ደግሞ አገልጋዩን መታገስ ሲያቅተው ፣ አማኝ ከአማኝ ጋር ዘይቅርታ መኖር ሲያቅተው ቀላሉ መንገድ መለየትና መለያየትን አደረገው።

በእርግጥ በአንዳንድ ትዳር ውስጥ ለህይወት የሚያስጋ ጥቃት እንዳለ የታወቀ ነው። ብዙ ሚስቶች በሰለጠነው አለም እንኳን እየኖሩ በባሎቻቸው የሚደበደቡ ፣ መሳሪያ ፊታቸው ላይ ደቅኖ የሚያስፈራራ ባል ያላቸውና ዘቅንአት ምክንያት ከማንም ሰው ጋር እንዳይገናኙ የታሰሩ እህቶችና ወንድሞች አጋጥመውኛል።

ሌሎችም ብዙ ስድብና ንቀት እንዲሁም የትዳር ገጽታ የሌለው ትዳር የሚኖሩ ለምን አገባሁ? የማግባቴ ትርጉም ምን ድን ነው? የሚሉ በየቤቱ ብዙ እንዳሉ እሙን ነው። ከዚህም በላይ የማያምን ባል ወይንም ሚስት ያላቸው በምንም ጉዳይ መግባባት አያቃታቸው ጌታ መቼ ነው? ከዚህ የሚያወጣኝ የሚሉ ብዙ ናቸው።

ታድያ ለዚህ መፍትሄው ምን ይሆን? መፋታት? መፋ ታትማ አይሆንም። እኛ ዘደም የተዋጀን የእግዚአብሔር መን





ፈስ ማደሪያ የሆንን በፊቱ ወድቀን ትዳራችን ከወዴት እንደ ወደቀ ብንጠይቀው ጌታ ይናገረናል። እልያም በህይወታችን ሊሰራ ያሰበውን እስኪጨርስ ድረስ በትእግስት እንጠብቃለን እንጂ መፋታትን መፍትሄ አድርገን ልንወስደው ፈጽሞ አይገባም።

ምን አልባት ካቅም በላይ የሆነ የማይገባ ሥነምግባር ከባል ወይ ከሚስት ቢታይ ለተወሰነ ጊዜ በመለያየት መፍትሄውን በጾምና ጸሎት በእግዚአብሔር ፊት ቀርቦ መፈለግ ይቻል ይሆናል። ይህም መንገድ እንኳን ቢሆን ተጋቢዎቹ እን ዳሰቡትና እንደፈለጉት የሚያደርጉት ሳይሆን ቤተክርስትያን ምክንያቱን አይታ በቂ ነው እስካለች ድረስ ብቻ መሆን ይኖርበታል።

ችግሩ ከዚህም አልፎ ቤተክርስትያን እንኳን ችግሩን በእግዚአብሔር ቃል መዝና ምክንያቱ ለፍቺ ያበቃል ብትል እን ኳን የእግዚአብሔር ጸጋ የበዛለት ሰው ግን የትዳር ጓደኛው በህይወት እስካለች ድረስ ሌላ ሴትን ባያገባ መልካም ነው። ሃዋርያው ጳውሎስ እንዳለው ግን ስለ ዝሙት ጠንቅ ምክንያት ከሚስቱ የተለያየ ወይንም ከባልዋ የተለያየች ሴት የእግዚ አብሔር ቃል በሚፈቅደው መንገድ ብቻ እንደገና ማግባት ይቻላል።

ይህን መሰል ጥያቄ ለጌታ እየሱስ በፈሪሳውያን ቀርቦለት ነበር። ሰው በማንኛውም ምክንያት ሚስቱን ሊፈታ ተፈቅ ዶለታልን? ሙሴ እንዲፈታት ጽፎለታል። አንተ ምን ትላለህ? ባሉት ጊዜ ሙሴ ስለ ልባችሁ ጥንካሬ ይህንን ጻፈላችሁ ፣ ከመጀመሪያው ግን እንዲህ አልነበረም በማለት ለመፍታት ምክንያት ያለውን ሰው የሚፈታበት ምክንያት ቢኖረውም እን ኳን ከመጀመሪያው እንዲህ እንዳልነበረና ይህ የእግዚአብሔር

የመጀመሪያና ዋነኛ ሃሳብ እንዳልሆነ ገልጾአል። (ማቴዎስ 19፥3-12)

ይህ የእግዚአብሔር የመጀመሪያ የጋብቻ እቅድ ወይም ፕላን ሰው እናቱንና አባቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተ ባበራል። ሁለቱም አንድ ስጋ ይሆናሉ። ከእንግዲህ አንድ አካል ናቸው እንጂ ሁለት አይደሉም። እንግዲህ እግዚአብሔር ያጣመረውን ሰው አይለየው ፤ በማለት መልስ ሰጥቶአል። ይህም የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ሃሳብ ባልና ሚስት አንድ ናቸው ፤ ለዘላለምም አንድ ይሆናሉ የሚል ነው። አራት ነጥብ።

ሃዋርያው ጳውሎስም በ1ኛ ቆሮንቶስ 7፥39-40 ድረስ ምንም እንኳን ባልዋ በሞት የተለያትን ሴት እንደገና አን ድታገባ ህጉ ነጻ ቢያደርጋትም እንኳን ሳታገባ ብትኖር ይበልጥ ደስተኛ ትሆናለች በማለት የትዳርን አንድ ሰው ለአንድ ብቻ እንደ ሆነ አጥብቆ ያስገነዝባል።

ይህን ስል አላማዬ መጽሐፍ ቅደስ በሚፈቅደው መንገድ እንደገና ያገቡትን ሰዎች ጋብቻቸው ስህተት ነው ለማለት ሳይሆን ፣ በየምክንያቱ ዘለው ከጋብቻ ለመውጣት ሰዎች የሚያቀርቡትን ምክንያት በማየትና ጋብቻ ክቡርነቱን እንዳያጣ የእግዚአብሔር የመጀመሪያ አላማ አንድ ሰው ለአንድ ብቻ የሚለውን አጉልቶ ለማሳየት ነው።

አንዳዶች ይህንን ጹሁፍ ሲያነቡ ያልተነካ ግልግል ያውቃል ሊሉኝ እንደሚችሉ ጥርጥር የለኝም። እስቲ አንድ ጥያቄ ለአንባቢዎቼ ልጠይቅ ፤ በትዳር ውስጥ ኖሮ የትዳር ችግር እሳት ወላፈን ያልለበለበው ማን ነው? አይነቱና ቅርጹ ይለያይ እንጂ ሁላችንም በትዳር ችግር ውስጥ እናልፋለን። ችግር ግን ጠንካራ እንጂ መራራ ሊያደርገን አይገባም።





ለመሆኑ ሳይመታ ያሸነፈ ቦቅሰኛ ማን አለ? ሳያልበው ሮጦ ያሸነፈ ማን የማራቶን ሯጭ አለ? ትኩረታችን በጡጫ የተመታነው ምት ላይና የሚያልበው ላብ ላይ ከሆነ እዎ በርግጥ ችግራችን ችግር ነው። ትኩረቱ ግን ሊሆን የሚገባው እንዴትና መቼ ያችን ገመድ በጥሼ ድል አገኝአለሁ የሚል ከሆነ የተመታነው ምት ወይም ያለበን ላብ ፈጽሞ አይሰማን ም። ላቡም ይደርቃል ቁስሉም ይድናል። መልእክቱ አንድና አጭር ነው በትዳር ውስጥ እንዴ ከገባችሁ ፍችን አታስቡት ነው።

> «ችግር ጠንካራ እንጂ መራራ ሊያደርገን አይገባም።»

ችግር ካለብን መውጫው መንገድ እየሱስ እንጂ ፍቺ አይደለም። ይህንን ሃሳብ ጌታ ኢየሱስ አስረግጦ በተናገረ ጊዜ ደቀመዛሙርት እንዲህ ከሆነ መጋ ባት አይጠቅምም አሉት። ጌታ ግን አይቦአችሁ በማለት አላጽ ናናቸውም። በሰው ዘንድ የማይ ቻል በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ ይቻላል ብሎ ዘግቶታል።

ከዚህ ሃሳብ እንደምንረዳው ትዳር በራስ ጀብደኝነት ወይንም በስሜት ላይ ተመስርተን የምንጀምረው ጉዞ ሳይሆን በጌታ ታምነን ጌታን ይዘን በጌታ ሁሉን ቻይነት ላይ ብቻ ተደግፈን ከጌታ ጋር የምንጨርሰው የህይወት ጎዳና መሆኑን ነው።

ትዳር ጣፋጭ ፍሬ ያለው የህይወት እርሻ ነው። ትዳርን ስናስብ መውጫችንን አዘጋጅተን ሳይሆን እግዚአብሔርን ታምነን እንግባ። ያን ጊዜ እግዚአብሔር እኛንና ትዳራችንን ካረሰ በኋላ ከትዳር የሚገኘውን ፍሬ እንበላለን።

ሚስት ከእግዚአብሔር የተገኘች ስጦታ ብትሆንም ቅሉ እግዚአብሔር ሚስት ስላገባህ ብቻ አይባርክህም። በትዳርህ ውስጥ እንደ በረከው የዘር አይነትና እንደ ድካምህ ይባርክሃል እንጂ። በሚስትህ ላይ ፍቅርን ከዘራህ ፍቅርን ታጭዳለህ። መገዛትን ካሳየሃት ትገዛልሃለች። ከታዘዝካት ትታዘዝሃለች። ሰው ካልዘራ በት ያጭድም። ካልበተነበት አይሰበስብምና። ይህ ለሁሉ ለወንድም ለሴትም የሚሰራ የህይወት መመሪያ ነው።

**«ትዳር ጣፋጭ ፍሬ ያለው የህይወት እርሻ ነው። ትዳርን ስናስብ መውጫችንን አዘጋጅተን ሳይሆን እግዚአብሔርን ታምነን እንግባ። ያን ጊዜ እግዚአብሔር እኛንና ትዳራችንን ካረሰ በኋላ ከትዳር የሚገኘውን ፍሬ እንበላለን።»**

ይህ የጋብቻና የፍቺ ጥያቄ እንዲህ በቀላሉ በጥቂት ገጾች ላይ በማሰፈር መልስ ይገኝለታል የሚል ሃሳብ የለኝም። የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች ለረጅም ዘመን የሚከራከሩበትንና ስፊ ትንተና የሚሰጡበትን እኔ በአጭር ቃል መልሱ ይሄ ነው ብዬ ለመዝጋት መሻቴ አይደለም።

ከዚህም በላይ የማንንም ጋብቻ ትክክል ነው ወይንም ትክክል አይደለም ማለት አላማዬ አይደለም። እግዚአብሔር በዚህ ወንበር ላይ ማንንም አላስቀመጠምና። ይሁን እንጂ ልን ክደው የማንችለው የቃሉ እውነት ስላለ ይህንን ሃሳብ ለመቋጨት ያህል እንዲህ ልበል።

የጋብቻ ፍቺ በሰው ሃጢአትና በደል ምክንያት የመጣ እንጂ የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ሃሳብ ፈጽሞ አይደለም።





የትኛውም ዘመን የትኛውም ሰልጣኔና ልክ የሚመስል የሰዎች የህይወት ልምምድ ይህንን እውነት ሊሽረው አይችልም። ለፍቺ የሚያበቃ አጥጋቢ ምክንያትም ይኑር ወይንም አይኑር ፍቺ የእግዚአብሔር ሃሳብ አይደለም። ሊሆንም አይችልም። ከእው ነት የሆነ ሁሉ እውነትን ይሰማል ስለ እውነት እንጂ በእውነት ላይ ምንም ማድረግ አንችልምና።

ይህ ትውልድ በእግዚአብሔር ቃል እውነት ላይ የሚራመድ ፣ በእግዚአብሔር እውነት የእግዚአብሔርን መን ግስት የሚያሰፋ እንዲሆንና የእግዚአብሔር መንግስት የጨለ ማውን መንግስት እንዲሰብረው ፍችን እየተቃወምን እግዚ አብሔራዊ ቤተሰብን መገንባት የቤተክርስትያን ከመጨረሻ ዘመን ተልእኮዋ መካከል አንዱ ሊሆን ይገባል። ቤተሰብን ሳን ሰራ ቤተክርስትያንን ልንሰራ ፈጽሞ አንችልምና።

የእኔ ጸሎት በቤተክርስትያን ውስጥ እረኞች ፣ ወን ጌላውያን ፣ አስተማሪዎች ፣ ሃዋርያትና ነቢያት እንዳሉ ሁሉ የቤተሰብ እረኞች የቤተሰብ አስተማሪዎችና በቤተሰብ ዙሪያ የተለያዩ ሚኒስትሪዎች እንዲነሱ ነው። ጌታ እግዚአብሔር አምላክ ይህንን በምድራችንና በአለም ዙሪያ ያድርግ።